# በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የ1990 የጤናና አመጋ ገብ ጥናት የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ

1 መግቢያ

የጤናና አመጋገብ ችግሮች እና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለማስወገድ በ ቅድሚያ የችግሮቹን ዓይነት፣ ጥልቀትና ስርጭት ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ወቅታዊና ተከታታይ ጥናቶች መካሄድ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም የተለያዩ ፕሮጀክቶችና ፕሮግ ራሞች በሕብረተሰቡ የአመጋገብና ጤንነት ላይ ያስከተሉትን ውጤቶች ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችሉ መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው። ነገር ግን ጤናና አመጋገብን በሚመለከት ለጊዜው ያሉት መረጃዎች ውሱን በመሆናቸው የተቀናጀ የቤተሰብ ሰር ቬይ ፕሮግራም አካል የሆነ የጤናና አመጋገብ ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ።

2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዋና ዓላማዎች የሕዝቡን የጤንነትና የአመጋገብ ሁኔታ ለማ ሻሻል በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ ለሚታቀዱትና ለሚቀየሱት የጤናና አመጋገብ ፕ ሮጀክቶች መሠረት የሚሆንና እንደዚሁም የሕዝቡን የጤንነትና የአመጋገብ ሁኔታ ለ ማሻሻል የሚዘረጉትን ፕሮግራሞች ሂደት ለመከታተልና ለመገምገም የሚረዱ መረጃዎ ችን ለማስገኘት ናቸው።

በአጠቃላይ ለማካሄድ የታቀደው ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችን ያካ ትታል:-

2.1 በተለያዩ አካባቢዎች የበሽታዎች ዓይነትና ስርጭት እንዲሁም የአደጋዎችን ስርጭት ለማሳየት የሚረዱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣

2.2 ሰዎች በታመሙ ጊዜ የሕክምና እርዳታ ለማግኘት የት እንደሚሄዱ ወይም ምን እንደሚያደርጉ ለማወቅና ታመው የሕክምና እርዳታ ያላገኙበት ምክንያት ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ማግኘት፣

2.3 ዘመናዊ የጤና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን በሚመለከት ሕዝቡ ያለውን አስተያየት ለመግለጽ ከመርዳቱም በላይ በአሁኑ ጊዜ ለሕዝቡ የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ከሕዝቡ ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚመጣጠን ማሳየት፣

2.4 ወሳድ ሴቶች በሚወልዱበት ጊዜ በምን ዓይነት የማዋለጃ አገልግሎት እንደሚጠቀሙ ለማወቅና ዘመናዊ የሕክምና ክትትል የሚያደርጉ ስለ መሆናቸውን የሚያመለክት መረጃ ለመሰብሰብ፣

2.5 የአመጋገብ ችግሮችንና ስርጭት ለማወቅና እነዚህንም ችግሮች ለማሻሻል የሚያስችሉ መርሀ ግብሮችን ለመቅረጽ መሠረት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣

2.6 የአመጋገብ ችግር ጎልቶ የሚታይባቸውን አካባቢዎች/የህብረተሰብ ክፍሎች ለይቶ በማወቅ ለሚመለከታቸው የዕቅድ አወሳሰድና አስፈጻሚ ዘርፎች ማን፣ የት፣ ለምን የአመጋገብና ከዚሁ ጋር ተዛማጅ ችግር እንዳለበት ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

2.7 ነፍሰጡር ሴቶች፣ ሕፃናትና ትናንሽ ልጆች ክትባቶች የሚያገኙ ወይም የማያገኙ ስለመሆናቸው የሚያመለክቱ መረጃዎች ማግኘት፣

2.8 ዕድሜያቸው ከ3ወር እስከ 59 ወር ለሆናቸው ሕፃናት ስለጡት ማጥባት መረጃ መሰብሰብ፣

2.9 በአመጋገብ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው የቤተሰብ አባላት/የሚያጠቡ እናቶችና ነፍሰጡር ሴቶች ሕፃናት፣ ትናንሽ ልጆች/ ተጨማሪ ምግብ ያገኙ ወይም አያገኙ እንደሆነ ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎችን መሰብሰብ።

2.10 በሚሰበሰቡ መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ የተለያዩ ፕሮጀክቶችና መርሀ ግብሮች በሕብረተሰቡ የአመጋገብና የጤንነት አቋም ላይ ያስከተሉትን ውጤቶች ለመከታተልና ለመገምገም ናቸው።

3. <u>በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች</u>

በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ርዕሶች ሊጠቃለሉ ይ ችላሉ።

3.1 የተወሰኑ የማኅበራዊና ዲሞግራፊያዊ ሁኔታዎች፣
3.2 ባለፉት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት ላይ ስለደረሱ በሽታዎች፣
3.3 በበሽታ/አደጋ ምክንያት የዘወትር ተግባር ስለማቋረጥ፣

3.4 ባለፉት 14 ቀናት ስለደረሱ አደጋዎች፣

3.5

ባለፉት 12 ወራት በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት በቤተሰቡ አባላት ላይ ጉዳት መድረሱ አለመድረሱ፣

3.6 ባለፉት 12 ወራት ጉዳት የደረሰባቸው አባላት የሕክምና እርዳታ የማግኘት ሁኔታና ስለዘመናዊ የሕክምና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ያላቸው አመለካከት፣

3.7 እናቶች ሲወልዱ ማን እንዳዋለዳቸውና በእርግዝና ወቅት ዘመናዊ ሕክምናና ክትባት ስለመውሰዳቸው፣

3.8 ሕፃናት ክትባትና ቪይታሚን ኤ እንክብሎች ስለመወሰዳቸው፣

3.9 ባለፉት 14 ቀናት ሕፃናት ተቅማጥ፣ ትውከትና ሳል ስለመታመማቸውና ታመው ምን እንደተሰጣቸው፣

3.10 የሕፃናት ጡት የማጥባት ሁኔታ፣

3.11 የተጋለጡ በመሆናቸው በአመጋገብ በኩል ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው የቤተሰብ አባላት ተጨማሪ ምግብ ስለመመገባቸው፣

3.12 ዕድሜያቸው ከ3-59 ወራት ለሆኑ ልጆች የቁመትና ክብደት ልክቶሽ፡፡

4. <u>የመጠይቁ አሞላል መመሪያ</u>

1. <u>መረጃ ሰብሳቢው በሚካሄድበት ቤተሰብ ተገኝቶ ተግባሩን ሲፈጽም የሚያሳያቸው የቅድመ ሁኔታዎች</u>

1.1 ማንኛውም መረጃ ሰብሳቢው ጥናቱን ለማካሄድ ከተመረጡ ቤተሰብ ወይም ቤት ሲደርስ ሰላምታ በመስጠት፣ ቀጥሎ ራሱን ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር በማስተዋወቅና የመጣበትን ዓላማ በማስረዳት መጀመር ያስፈልጋል፡፡ ቀደም ሲል በገጽ 1 የተገለጸው የጥናቱን ዋና ዓላማ ለቤተሰቡ በሚገባ መንገድ ማብራራትና መግለጽ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

1.2

ይህ ጥናት በአንድ ቤተሰብ በሚካሄድበት ጊዜ የቤተሰቡ ኃላፊ መገኘት ያለበት ሲሆን በተቻለ መጠን የቀሩትም የቤተሰቡ አባላት መገኘት አለባቸው፡፡ ዋናው ተጠያቂ ወይም መልስ ሰጭ የቤተሰቡ ኃላፊና ሚስት/ባል ሲሆኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች አባልንም ሲጠየቁና መልስ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ አንድ በሽታ የደረሰበት አባል በሽታው እንዴት እንደሚያደርገው ከ ኃላፊው ይበልጥ አባሉ ማስረዳት ይችል ይሆናል።

–

1.3 ጥናቱ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ በሚካሄድበት ጊዜ የቤተሰቡ አባላት ያልሆኑ እንደ ጎረቤት፣ ወዳጅ፣ ዘመድ...ወዘተ የመሳሰሉ ሰዎች መገኘት የጥናቱን ጥራት ስለሚቀንሰው የቤተሰቡ አባላት ብቻ ባሉበት መጠይቁ ቢደረግ ለሥራው ጥራት ጥሩ ይሆናል።

2. <u>በአጠቃላይ እያንዳንዱ ዓምድ ሲሞላ በጥንቃቄ መሞላት አለበት</u>

2.1 መልሱ በቃላት ብቻ የሚጻፍ ከሆነ በዚያ ዓምድ ውስጥ ለኮድ በተሰጠው ቦታ ውስጥ መጻፍ የተከለከለ ነው።

2.2 በአጠቃላይ የመረጃዎቹ አመዘጋገብ በጥራት (ጽሑፉ በደንብ የሚነበብ፣...) መሆን አለበት፣

2.3 የሚፈለገው መልስ በኮድ የሚጻፍ ከሆነ ትክክለኛውን ኮድ በመምረጥ በተገቢው ቦታ መጻፍ ያስፈልጋል።

<u>ክፍል 1፡- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ</u>

<u>ዓምድ 1-10 የአካባቢ መለያና ቤተሰቡን የሚመለከት ሌሎች መረጃዎች</u>

ይህ ክፍል ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ ዞን፣ የወረዳ፣ የከፍተኛ/ወረዳ፣ ቀበሌ/ገበሬማኅበር ስም፣ የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር፣ የቤተሰብ አባላት ብዛት ናየቤተሰቡ ኃላፊሙሉ ስም የሚመዘገብበት ነው።

<u>ዓምድ 1፡- ክልል</u>

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ክልል ስም ይሞላል። በካረድ ኮለሞች ውስጥ ምንም አይሞላም።

ዓምድ 2:- ዞን

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ዞን ስም ይሞላል:: በካርድ ኮለም ውስጥ ምንም አይሞላም::

ዓምድ 3:- ወረዳ፡

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ወረዳ ስም ይሞላል:: በካርድ ኮለም ውስጥ ምንም አይሞላም::

ዓምድ 4:- ከተማ

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ከተማ ስም ይሞላል:: ጥናቱ በገጠር የሚካሄድ ከሆነ "ገጠር" የሚለው ቃል በዓምድ ይስፍራል:: በካርድ ኮለም ውስጥ ምንም አይሞላም::

ዓምድ 5:- ከፍተኛ/ወረዳ

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ከፍተኛ/ወረዳ ስም ይሞላል::

ዓምድ 6:- ቀበሌ/ ገ/ማህበር

ጥናቱ የሚካሄድበትቆጠራ ቦታ የሚገኝበት ከተማ ከሆነ የቀበሌ ቁጥር በተሰጠ ው ክፍት ቦታና በካርድ ኮለሞቹ ውስጥ ይመዘገባል:: ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦ ታ የሚገኝበት ገጠር ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ የገ/ማህበር ስም ይመዘገባል::

ዓምድ 7:- የቆጠራ ቦታ ኮድ፡

ጥናቱ የሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ ኮድ በካርድ ኮለም ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 8:- የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር፡

ይህ ዓምድ ለጥናቱ የተመረጡትን ቤተሰቦች ተራ ቁጥር እንደ አመራረጣቸው ቅደም ተከተል የሚያሳይ ነው:: ስለሆነም በመጀመሪያ ለተመረጠው ቤተሰብ "01" የሚል ተራ ቁጥር ተሰጥቶት በሁለተኛ ለተመረጠ "02"

በመመዝገብ የቤተሰቦቹ ተከታታይ ተራ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሰፍራል::

የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር ከመመዝገቢያ ቅጽ /90 በመውሰድ የሚሞላ ይሆናል::

ዓምድ 9:- የተመረጠው ቤተሰብ አባላት ብዛት፡

በቅድሚያ "ቤተሰብ" ማለት ምን ማለት መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ ሁልጊዜ አብረው የ ሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ማዕድ ቤት አብስለው በአንድነት የሚመገቡትን ሰዎ ች ያጠቃልላል፡፡ የቤተሰብ አባሎች በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዘመዱትን ሊያጠቃል ል ይችላል፡፡ በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች የባል ወይም የ ሚስት አባት፥ እናት፥ እህት ወንድም ሲሆኑ በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱት የ ቤተሰብ አባሎች ዘበኞች፥ የቤት ሠራተኞች፥ ጥገኞች ወዘተ… ናቸው፡፡

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል፡፡ ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እ ንደ አንድ ቤተሰብ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ወይም ሌሎች ሰዎች እንደ ዘበኞች፥ ጥገኞች ወዘተ… ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚኖሩና በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ በ ተሰበ ይወሰዳሉ፡፡ ነገር ግን ጥናቱ ከሚፈፀምበት ቀን በፊት ቤተሰቡን ትቶ በእንግድ ነት ወደ ሌላ ቤተሰብ ሄዶ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀመጠ በኋላ አሁን ለሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ ለቤተሰቡ አባል ይሆናል ማለት ነው፡፡ ጋ ብቻው በአንድ ሚስት ላይ ብቻ የተመሠረተ ከሆነ አንድ ቤተሰብ ባልን፥ ሚስትን፥ ልጆችን፣ የጉዲፈቻ ልጆችን፥ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን /የቤት ሠራተኞ ች …ወዘተ/ ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠ ረተ ከሆነ/ ማለት አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚሰቶች ካሉት/ የሰውየው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው …ወዘተ በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የማይ ኖሩ፥ ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የማይበሉ ከሆነ፥ እያንዳንዳቸው የሰውየው ሚስቶች እንደ የተለየ ቤተሰብ መወሰድ አለባቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ ባልየው አሁን ካ ለችው አንጋፋ ሚስቱ ጋር እንደ ቤተሰብ አባል ሲቆጠር፥ ሁለተኛ፥ ሶስተኛ ወዘተ… ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ ስለአላቸው ከልጆቻቸውና ከቀሩት ጥገኞቻቸው ጋር ለየራሳቸው እንደ ቤተሰብ ይመዘገባሉ፡፡ ከቤተሰብ ትርጉም በተጨማሪ ቀጥሎ ያሉትን ዓምዶች ለመሙላት "መደበኛ የቤተሰብ አባላት" ትርጉም ማብራራት ተገቢ ይሆናል፡ ፡

በዘሁ መሠረት አንድ ሰው "መደበኛ የቤተሰብ አባል" ነውየሚባለውቢያንስ ስ ድስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከቤተሰቡ ጋር የኖረ እንደሆነ ነው፡፡ ከቤተሰቡ ጋር ለዘ ለቄታው ለመኖር የመጡ ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸ ውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል ይቆጠራሉ፡፡ ከስድስት ወር በታች ከቤተሰቡ ለጊዘ ው ተለይተው የቆዩ የቤተሰብ አባላት እንደ መደበኛ የቤተሰቡ አባል መቆጠር አለባ ቸው፡፡ ነገር ግን ከቤተሰቡ ተለይተው ከሄዱ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸ ው፣ ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት አቅደው የሄዱ ከቤተሰቡ ከወጡ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠሩም፡፡

## የሚከተሉት የቤተሰብ አባላት እንደመደበኛ የቤተሰብ አባል መቆጠር ይኖርባቸዋል::

ሀ. አብዛኛውን ጊዜ /ስድስት ወርና በላይ/ ከቤተሰቡ ጋር የኖረ ይመዘገባል::

ለ.

አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ፥ በጥናቱ ቀን ለጥቂት ጊዜ /ከ ስድስት ወር ያነሰ/ ከቤተሰቡ የተለዩ ሰዎች ለተለዩበት ቤተሰብ አባሎች ይሆናሉ:: ለምሳሌ በዕረፍት ላይ ያሉትን፥ ለዓመት በዓል ወ ደ ሌላ ቦታ የሄዱትን፥ ዘመድ ለመጠየቅ የተጓዙትን፥ ለጥቂት ጊዜ ሆስፒታል የሚቆዩትን፥ በሥራ ምክንያት በጉዞ ላይ ያሉትንና የመሳሰ ሉት ናቸው::

ሐ.

አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ የቤት ሠራተኞች፥ ዘ በኞች፥ የቀን ሠራተኞች .... ወዘተ ሌላ መኖሪያ ቤት ከሌላቸው ከሚሠሩበት ቤተሰብ ጋር አባላት ይሆናሉ::

መ.

በአጠቃላይ አንድ ሰው ከአንድ ቤተሰብ ጋር ለስድስት ወር ወይም ከስ ድስት ወር በላይ ከቆየ፥ ይህ ሰው በተጠቀሰው ቤተሰብ እንደ ቋሚ ወይም መደበኛ አባል ይመዘገባል::

ሠ.

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከስድስት ወር በ ታች የተቀመጡ ከሆነ፥ እነኚህ ሰዎች ሌላ መኖሪያ ከሌላቸው በጥናቱ ቀን ከ ተገኙበት ቤተሰበ ጋር አባሎች ይሆናሉ ማለት ነው:: ለምሳሌ አንዲት ሴት ልጅ አግብታ ከወላጆችዋ ቤት ተለይታ ወደ ባሏ ቤት ስትሄድ ስድስት ወር ባ ይሞላትም እንኳን ከባሏ ቤተሰብ ጋር መመዝገብ አለባት::

በዚህ መሰረት የቤተሰብ ትርጉም ተለይቶ ከታወቀ በኃላ የተመረጠው ቤተሰብ መደበኛ አባላት ብዛት ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለም 21 እና 22 ውስጥ ይሞ ላል::

ዓምድ 10:- የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም፡

በዚህ ዓምድ የተመረጠው ቤተሰብ ኃላፊ መሉ ስም ይመዘገባል። የቤተሰብ ኃላፊ ማለት የአንድ ቤተሰብ መደበኛ አባል የሆነ ወንድ ወይም ሴት በቤተሰቡ አባላት እንደ ኃላፊ የሚቆጠር ወይም የሚታይ ነው። ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ሰው ሚስቶቹ በተለያየ ቤተሰብ የሚኖሩ ከሆነ እሱ የቤተሰብ ኃላፊ ሆኖ የሚመዘገበው አሁን በህይወት ካሉት ውስጥ በቅድሚያ ካገባት (አንጋፋ) ሚስቱ ጋር ይሆናል። ሌሎች የሰውየው ሚስቶች ግን የየራሳቸው ቤተሰብ ኃላፊ/አባል ሆነው ይመዘገባሉ።

ክፍል 2:- የቤተሰቡ የጤና ሁኔታ (ለሁሉም የቤተሰብ አባላት የሚጠየቅ)

ዓምድ 11:- ተራ ቁጥር፡

ይህ ዓምድ ብዛታቸው 10 ወይም ከዚያ በታች የሆኑ የቤተሰብ አባላትን ለመመዝገብ ተዘጋጅቷል።

ነገር ግን የቤተሰቡ አባላት ቁጥር ከ10 በላይ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ ፎርሞች እንደ አስፈላጊነቱ በመጠቀም በተጨማሪው ፎርም ከዓምድ 1-10 ያለውን ከመጀመሪያው ፎርም በመገልበጥ ይሞላል። ከዚያም ዓምድ 11 ላይ ከዚህ በፊት የታተመውን ተራ ቁጥር 01፣ 02፣ 03፣ ...ወዘተ. ሰርዞ 11፣ 12፣ 13...ወዘተ.በማድረግ መለወጥ አለበት። በተጨማሪም በመጀመሪያ ገጽ ግረጌ ጎላ ባለ ጽሑፍ " የሚቀጥል" ሲመዘገብ፣ በቀጣዩ ገጽ አናት "የቀጠለ" ይጻፋል።

ዓምድ 12 - መደበኛ የቤተሰቡ አባላት ሙሉ ስም፡

በዚህ በዓምድ የቤተሰቡ መደበኛ አባላት የሆኑት ሙሉ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል። ምዝገባ በሚከናወንበት ጊዜ በመጀመሪያ መስመር የቤተሰቡ ኃላፊ፣ በሁለተኛው ሚስቱ /ባልየው/፣ በሦስተኛው ያላገቡ ልጆች /በዕድሜ ቀደም ተከተል/፣ ቀጥሎም ያገቡ ልጆች /ከቤተሰቡ ጋር አብረው የሚኖሩ ማለት ቋሚ አባሎች ከሆኑ፣/ ዘመዶቻቸው፣ ጥገኞቻቸው፣ ሠራተኞቻቸው፣ ወዘተ... ይመዘገባሉ። ይህ ዓ

ምድ በሚሞላበት ወቅት ለመደበኛ የቤተሰብ አባላት በዓምድ 9 የተሰጠውን ማብራሪ ያ ማስታወስ በጣም አስፈላጊ ነው።

<u>ማሳሰቢያ፡</u> በቅርብ ጊዜ የተወለደ ሕፃን ልጅ ካለ ሳይረሳ መመዝገብ ይገባል። ሕፃኑ ገና ስም ያልወጣለት ከሆነ "ሕፃን" በማለት ይመዘገባል።

<u>ዓምድ 13፡- ጾታ</u>

በዓምድ 11 ስማቸው ከተመዘገበው መደበኛ የቤተሰብ አባላት ስም አንፃር ፆ ታቸው ተጠይቆ በካርድ ኮለም 25 ትክክለኛው ኮድ ይሞላል። ለምሳሌ የአባሉ ፆታ ወንድ ከሆነ ኮድ "1" ሴት ከሆነች ኮድ"2" በስማቸው አንፃር ይመዘገባል። የአንዳንድ ሰዎች ስም ለሁለቱም ፆታዎች ሊያገለግል ስለሚችል የአባላቱን ስም ብቻ መሰረት በ ማድረግ ፆታቸውን በግምት መሞላት የለበትም። በአንዳንድ አካባቢዎች ወንድ በሴት ስም እንዲሁም ሴት በወንድ ስም ስለሚጠሩ ፆታ በሚሞላት ጊዜ ብርቱ ጥንቃቄ ማ ድረግ ያስፈልጋል። በተለይ የሕፃናት ፆታ ሲመዘገብ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላ ጊ ነው።

<u>ዓምድ 14 ዕድሜ</u>

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል መጠይቁ በሚሞላለት ጊዜ ያለው ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት (በጨረሱት ዓመት) በዚህ ዓምድ ይመዘገባል። ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለምሳሌ የአንድ ሰው ዕድሜ 15 ዓመት፣ ከ 5 ወር ከ11 ቀን ቢሆን መመዘገብ ያለበት 15 ዓመት ብቻ ይሆናል ማለት ነው። የ አንድ ሕፃን ዕድሜ ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ በዓምድ 14 ባሉት ካርድ ኮለሞች ኮድ "00"፣ አንድ ዓመት ሞልቶት ከሁለት ዓመት በታች ከሆነ ደግሞ "01" በማለት ይ መዘገባል። እንዲሁም አንድ ሰው ዕድሜው 98 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ "97" ብቻ በካርድ ኮለሙ ይመዘገባል።

ዕድሜያቸውን በትክክል የማያውቁ ወይም ዕድሜያቸውን ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች እንደሚያጋጥሙ ይገመታል። ስለዚህ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ትክክለኛ ዕድሜ በተቻለ መጠን ለማግኘት ያለመሰልቸት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስ ፈልጋል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚያስችሉት ዘዴዎች መካከል ቀጥሎ የተመ ለከቱትን ማጤን ይገባል።

መልስ ሰጪው በተወለደበት ጊዜ/አካባቢ በብሄራዊ ደረጃ ወይም በሚኖርበት አካባቢ የተፈፀመ ታሪካዊ ድርጊት እንዳለና ቀጥሎም መልስ ሰጭው ድርጊቱ በተፈፀ

መ ጊዜ ዕድሜው ምን ያህል እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ እንደተወለደ በመጠየቅና ከዚያም ይህንን መረጃ መሠረት በማድረግ የግለሰቡን ዕድሜ ለገመገት መሞከር ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ግለሰቡ የ1966 አብዮት ከመፈንዳቱ 10 ዓመት ቀድሞ የተወለደ እንደሆነ የግለሰቡ ዕድሜ በ1990 ዓ.ም. ከሞላ ጎደል (1990-1966)+10=34 ዓመት ተብሎ ይመዘገባል፡፡ ስለዚህ የአንድ ግለሰብ የተወለደበትን ዓመት ታሪካዊ ድርጊቶች ከተፈፀሙበት ዓመተ ምሕረት ጋር በማዛመድ ዕድሜውን ለመገመት ስለሚቻል ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈፀሙበት ዓመተ ምሕረት ዝርዝር በአዝል 1 ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡

አንዳንድ የቤተሰብ አባላት ወይም በአካባቢው የሚኖሩ ግለሰቦች ዕድሜአቸውን ሊያውቁ ይችሉ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ ዕድሜያቸውን የማያውቁትን ሰዎች ዕድሜ ከነዚህ ዕድሜያቸውን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል፡፡

ከቤተሰቡ አባላት መካከል የአንዱ ዕድሜ በትክክል ከታወቀ፣ የሌሎችን ዕድሜ ለመገመት ይቻል ይሆናል፡፡ ለምሣሌ የአንድ ቤተሰብ የመጀመሪያው ልጅ ዕድሜው 13 ዓመት መሆኑ ከታወቀና የእናቱን ዕድሜ ለማወቅ ቢፈለግ የእናቱ ዕድሜ ቢያንስ 29 ዓመት ብሎ ለመገመት ይቻላል፡፡ ይህም ሊገኝ የሚችለው እናቶች አብዛኛውን ጊዜ በ16 ዓመት የመጀመሪያውን ልጅ ይወልዳሉ ተብሎ ስለሚገመት የእናትየዋ ዕድሜ 16+13 = 29 ይሆናል፡፡ የሥጋ ሥምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የአንዱን ዕድሜ ከሌላው በማነፃፀር ዕድሜያቸውን ለመገመት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ እናቶች በየሁለት ዓመት ይወልዳሉ፡፡ የትንሹ ልጅ ዕድሜ 7 ዓመት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የታላቁ ልጅ ዕድሜ 9 ዓመት ሊሆን ይችላል፡፡ ዕድሜያቸው የገፉ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ዕድሜያቸውን በጣም ከፍ ያደርጉታል፡፡ የነኚህን ሰዎች ዕድሜ ከመጀመሪያው ልጃቸውና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የአንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ ከታወቀ ከሌላው አባል ጋር በማዛመድ በተቻለ መጠን ትክክለኛ የሆነውን ገምቶ መፃፍ ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም አንድ አባል ባገባበት ጊዜ ዕድሜው ስንት እንደነበረና በጋብቻ ስንት ዓመት እንደቆየ ከታወቀ ዕድሜውን ለመገመት ይቻላል፡፡

አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሃዞች ለመናገር ይፈልጋሉ ወይም ይቀላቸዋል፡፡ ስለዚህ ዕድሜያቸውን መግለፅ የሚገባቸው ለመናገር በሚቀላቸው ወይም በሚፈልጉት ሳይሆን፣ ትክክለኛውን ዕድሜ ለማግኘት መ

ሞከር ያስፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች በእርግጥ ዕድሜያቸው 10፣ 15፣ 20፣ 25፣... ወዘተ ሊሆን ይችላል።

በተለይ ዕድሜአቸው ከ5 ዓመት ያላለፉ ሕፃናት ልጆች የተወለዱበትን ጊዜ ወላጆቹ ሊያስታውሱት ስለሚችሉ የሕፃናትና ትናንሽ ልጆች ዕድሜ በሙሉ ዓመት በትክክል መፃፍ አለበት። አልፎ አልፎ የሕፃናትን ትክክለኛ ዕድሜ ለማግኘት ቀላል የማይሆንበት ሁኔታ ካጋጠመም ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ ትክክለኛውን ዕድሜ በማወቅ በትክክል መፃፍ ይኖርበታል።

ከዚህ በላይ የተሰጡትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ትክክለኛውን ዕድሜ ለማግኘት በቂ ጥረት አድርጎ ትክክለኛ መልሶችን ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማቅረብና በማስላት የእያንዳንዱ አባል ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት በዓምድ 14 ባሉ ካርድ ኮለሞች ይፃፋል።

<u>ዓምድ 15:- ሃይማኖት የ...... ሃይማኖት ምንድን ነው</u>

ሃይማኖት አንድ ግለሰብ የሚከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት ነው። የሃይማኖትን ዓይነት የሚመለከት ጥያቄ ለቤተሰቡ አባላት በሙሉ በማቅረብ ይህን መሙላት ያስፈልጋል። ሃይማኖት በሚጠየቅበት ጊዜ ክርስቲያን የሚል መልስ ከተገኘ ዓምድ 15 እግርጌ ከኮድ 1-3 ከተሰጡት የክርስቲያን ዓይነት ውስጥ <u>የትኛው ክርስቲያን መሆኑ ተጣርቶ</u>

ይሞላል። ስለዚህ በዓምዱ በተሰጠው ባዶ ቦታ እያንዳንዱ አባል የሚከተለውን ሃይማኖት በመጠየቅ ከዚህ በታች በተመለከቱት ኮዶች መሠረት መሞላት አለበት።

1. ኦርቶዶክስ
2. ፕሮቴስታንት /ለምሳሌ ሰባት ቀን አዲቬንቲስት፣ ጴንጤቆስጤና፣ ሉተሪያን፣ባፕቲስት፣መካናይት፣ መሶዲስት፣ፕሪስቢተርያን፣....ወዘተ./
3. ካቶሊክ
4. ሙስሊም/እስላም/
5. ባሕላዊ አምልኮ
6. ሌላ (ለምሳሌ:- ሂንዱ፣ ይሁዲ፣ በሃይ፣ ጆሆቫ፣ ኤቲስት...ወዘተ)

<u>ማሳሰቢያ፣</u> ባልና ሚስት የተለያየ ሃይማኖት ሊኖራቸው ይችላል። የተለያዩ ሃይማኖት ከሚከተሉ ወላጆች ለተወለደ ሕፃን ወደፊት ሊከተለው

ይችላል ብለው ወላጆች የሚያስቡትን ሃይማኖት በመውሰድ በዓምዱ ይሞላል።

ዓምድ 16፡- ብሔረሰብ፤

የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ብሄረሰብ ምን እንደሆነ ተጠይቆ በዓምድ 16 በካ ርድ ኮለም 29 እና 30 ትክክለኛው ኮድ ይመዘገባል። ግለሰቡ ብሄረሰብህ ምንድነው ተብሎ ሲጠየቅ ትርጉሙን ባለመረዳት ጥያቄውን በትክክል ለመመለስ ከተቸገረ ዘርህ ፣ ትውልድህ፣ ነገድህ፣ ጎሣህ በማለት በማብራራት ማስረዳት ያስፈልጋል። የብሄረሰቦች ን ስምና ኮድ በቀላሉ ለማግኘት እንዲያመች ሁለት ዝርዝሮች ማለትም "የዋና ዋና ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር" እና "የቅርንጫፍ ብሄረሰብ ስምና ኮድ ዝርዝር" በሚ ከተሉት ገፆች ላይ ቀርቦአል። ይህን በመገንዘብ የብሔረሰብ ስም ኮድ አመዘጋገብ እን ደሚከተለው ይሆናል።

1.

ለብሄረሰብ ኮድ መፃፊያ በተሰጠው ቦታ መልስ ሰጪው የሰጠው የብሄ ረሰብ ስም ኮድ ይመዘገባል። የብሄረሰባቸውን ስም ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ግለሰቦች ካጋጠሙ በተቻለ መጠን አግባብቶ ትክክለኛውን መልስ ማግኘት ያስፈልጋል።

2.

መልስ ሰጭው ለሰጠው ብሄረሰብ የተሰጠው ትክክለኛ ኮድ "የዋና ዋና ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር" በመመልከት በካርድ ኮለሞቹ ይመዘገባል። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ብሄረሰቡን ለማግኘት አስቸጋሪ ከሆነ ""የቅርንጫፍ ብሄረ ሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር በመመልከት ለማግኘት መሞከር በዝርዝሩ ውስጥ ያ ልተጻፈ ከሆነ ግን መልስ ሰጪው የሰጠው ብሔረሰብ ስም መጻፍ ይገባል።

3.

መልስ ሰጪው የሰጠው መልስ ዋናው/ግንድ ብሄረሰብ ወይም የግንድ ቅርንጫፍ ብሄረሰብ ሊሆን ይችላል። የተሰጠው መልስ ዋናው ብሄረሰብ ከሆነ የዋናው ብሄረስብ ኮድ የሚመዘገብ ሲሆን የተሰጠው መልስ ቅርንጫፍ ብሄረ ሰብ ከሆነ ግን ቅርንጫፍ ብሄረሰቡ የየትኛው ዋና ወይም ግንድ ብሄረሰብ አካ ል እንደሆነ በመለየት የሚሰጠው ኮድ የዋናው ወይም የግንድ ብሄረሰብ ኮድ ይሆናል። ለምሳሌ መልስ ሰጪው የሰጠው ብሄረሰብ ስም ሳይንቴ ቢሆን ግን

ጱ አማራ ስለሆነ በካርድ ኮለሙ የሚሞላው "04" ነው። ይኸውም የአማራ ብሄረሰብ መለያ ኮድ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ መልስ ሰጪው የሰጠው የብ ሔረሰብ ስም እነቆር ቢሆን ግንጱ ጉራጌ ስለሆነ በካርድ ኮለሙ "25" ይሞላል፡ ፡

## ሀ. የዋና ዋና ብሔረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር

በዚህ ዝርዝር ውስጥ ለአብዛኛው ብሄረሰቦች የቀረቡ ሲሆን አቀማመጣቸውም ዋና ዋና ብሄረሰቦችን በመጠቀም ነው። የዋናው ብሄረሰብ ሞክሼ ስሞችና ቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ከዋናው ብሄረሰብ ጋር ተመሣሣይ ኮድ ስለሚሰጣቸው በቅንፍ ውስጥ ቀር በዋል። ለምሳሌ አጳል፣ ዳናኪል፣ ደንከል፣ ጠጣል፣ የሚባሉ ቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ሁለ - አፋር በሚባል ዋና ብሄረሰብ ሥር የሚጠቃለሉ በመሆናቸው በዝርዝሩም ውስጥ አ ፋር እንደ ዋና ብሄረሰብ ተፅፎ ሌሎቹ በቅንፍ ውስጥ ቀርበዋል። የብሄረሰብን መረጃ በትክክል ለመመዝገብ እንዲያመች ተመሣሣይነት ያላቸው ብሄረሰቦች በተከታታይነት መመዘገብ አስፈላጊ በመሆኑ ከአንድ ዋና ብሄረሰብ ጋር ተመሣሣይነት ያላቸው ብሄ ረሰቦች ሁሉ ዋነኛውን ብሄረሰብ ተከትለው በዝርዝሩ ላይ ትንሽ ገባ እየተደረጉ የቀረ ቡ ሲሆን ለነዚህም የራሳቸው የተለየ ኮድ ተሰጥቷቸዋል። ለምሳሌ ዶርዜ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ኮንታ፣ ኩሎ፣ እና ኮንታ የሚባሉ ብሄረሰቦች ከወላይታ ብሄረሰብ ጋር በጣም ስለሚቀ ራረቡ በዝርዝሩም ውስጥ ከወላይታ ቀጥሎ በተከታታይ ቀርበዋል። ነገር ግን እነዚህ ብሄረሰቦች ሁሉ ራሳቸውን የቻሉ የተለያዩ ብሄረሰቦች ስለሆኑ የየራሳቸው ኮድ ተሰጥ ቷቸዋል። ዋና ዋና ብሄረሰቦችን በቀላሉ ከዝርዝሩ ለማግኘት እንዲቻል አቀማመጣቸ ው የእንግሊዘኛውን ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ ነው።

## ለ. የቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ሥምና ኮድ ዝርዝር

ይህ ዝርዝር የተዘጋጀው "በዋና ዋና ብሄረሰቦች ሥምና ኮድ ዝርዝር" ውስጥ በቅንፍ ውስጥ የቀረቡትን ሞክሼ ስሞች ወይም ቅርንጫፍ ብሄረሰቦችን (ለምሣሌ፣ አጳ ል፣ ዳንኪል፣ ደንከል፣ ጠጣል) እንዲሁም በዝርዝሩ ላይ ትንሽ ገባ ብለው የቀረቡትን ብሄረሰቦች (ለምሣሌ፣ ዶርዜ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ኮንታ፣ ኩሎ፣ መሎ) በእንግሊዝኛ ፊደል ቅደ ም ተከተል መሠረት ለማቅረብ ነው። "በዋና ዋና ብሄረሰብ ሥምና ኮድ ዝርዝር" ው ስጥ ትንሽ ወጣ ብለው በእንግሊዘኛ ፊደል ቀደም ተከተል መሠረት የቀረቡት ዋና ዋ ና ብሄረሰቦች ግን (ለምሣሌ፣ አፋር፣ ወላይታ) በዚህኛው ዝርዝር ውስጥ በድጋሚ አ ልቀረቡም።

4.

ከተሰቀሱት ዋና ብሄረሰቦችና ቅርንጫፎች ማህበረሰቦች ውጭ ካጋጠሙ ለሌሎች የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የሚሰጥ ኮድ "90" ይሆናል፡፡

5.

ከሁለት የተለያዩ ኢትዮጵያውያን ብሄረሰቦች ወይም ከኢትዩጵያውያን ና ከውጭ አገር ዜጎች የተወለዱ ግለሰቦች ዕድሜያቸው 18 ዓመትና በላይ ከ ሆነ እነሱ የመረጡት የብሄረሰብ ኮድ በዓምዱ ይመዘገባል፡፡ ዕድሜያቸው ከ1 8 ዓመት በታች ከሆነ ግን ወላጅ ወይም አሳዳጊ የወሰነው የብሄረሰብ ኮድ በዓ ምዱ እንዲፃፍ ያስፈልጋል፡፡

6.

ከተለያዩ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ለተወለደና ከአባቱና ከእናቱ ብሄረስ ብ አንዱን ለይቶ ለመናገር ለማይፈልግ የሁለቱ ብሄረሰቦች ስም ተፅፎ ከተለያ ዩ ብሄረሰቦች የተወለዱ የሚለው ኮድ 91 ይሞላል፡፡ ከእናታቸው ወይም ከአ ባታቸው ብሄረሰብ አንዱን መርጠው ለመናገር ፈቃደኛ ለሆኑ ግን የመረጡት ብሄረሰብ ስም ተመዝግቦ የብሄረሰቡ ኮድ ይሞላላቸዋል፡፡

7.

ኤርትራዊያን ለሆኑ በዓምዱ "ኤርትራዊ" ተብሎ ተመዝግቦ ኮድ "93" በካርድ ኮለሞች ይመዘገባል፡፡ እንዲሁም ለጅቡቲያውያን ኮድ "94" ይሰጣቸ ዋል፡፡ ለሱማሊያ አገር ዜጎች "ሶማሊያዊ" ተብሎ ተመዝግቦ ኮድ "95" በካርድ ኮለሞቹ ይመዘገባል፡፡ ይህ ኮድ ግን የሚመዘገበው ኢትዮጵያውያን ላልሆኑ ብቻ እነደሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ለኢትዮጵያዊያን ሶማሌዎች የሚመዘገበ ው "ሶማሌ" የሚል መልስ ሲሆን የሚሰጣቸው ኮድ "68" ነው፡፡ ለኬንያውያ ን ኮድ 96፣ ለሱዳናዊያን ኮድ 97 የሚመዘገብ ሲሆን ለሌሎች የውጭ አገር ዘ ጋዎች ሁለ የአገራቸው ስም ተመዝግቦ ኮድ 98 ይሰጣቸዋል፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>

በቋንቋዎች ዝርዝር ላይ የተገለፁት ከ“A” እስከ “Z” ያሉት የእንግሊዝኛ ሆሄ ያት አንድን ቋነቋ በቀላሉ ከዝርዝሩ ለማግኘት እንዲረዱ የተጻፉ ናቸው እንጂ የቋን ቋ ኮድ በሚሰጥበት ወቅት አብረው የሚገለጹ አይደሉም፡፡ የዋና ዋና ብሔረሰቦችና የቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## ዓምድ 17-18:- ዕድሜያቸው አስር ዓመትና በላይ ለሆናቸው አባላት የሚጠየቅ፡

### ዓምድ 17:- ማንበብና መፃፍ ይችላሉ? ካልቻሉ "00" ከቻሉ ያጠናቀቁት ከፍተኛ ክፍል፡

ይህ ዓምድ ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ ለሆኑ የቤተሰብ አባላት ሁሉ መሞላት አለበት:: በመጀመሪያ ግለሰቡ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ እንዳላቸው ተጠይቆ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ከሆነ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ይጠየቃል:: የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ከሌላቸው በካርድ ኮለም 31 እና 32 ውስጥ "00" ይሞላል:: ነገር ግን የቤተሰቡ አባል የማንበብና መጻፍ ችሎታ ካላቸው የጨረሱትን ከፍተኛ ክፍል በመጠየቅ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ኮዶች ትክክለኛው ኮድ ተመርጦ በዓምድ 17 በካርድ ኮለም 31 እና 32 ውስጥ ይሞላል::

አንድ ግለሰብ የማንበብና መጻፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መጻፍ ሲችል ነው:: የራሳቸውን ስም ወይም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ግለሰቦች የማንበብና መጻፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም:: እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዓረፍተ ነገሮችን ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና መጻፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም::

00= ማንበብና መጻፍ የማይችል

01= የአንደኛ ክፍል ትምህርትን ላጠናቀቀና ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ሁሉ

02= የ2ኛ ክፍል ትምህርትን ላጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሁሉ፤

03= የ3ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሁሉ

04= የ4ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ሁሉ

05= የ5ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ሁሉ

06= የ6ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ሁሉ

07= የ7ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ሁሉ

08= የ8ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ሁሉ

09= የ9ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ሁሉ

10= የ10ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ሁሉ

11= የ11ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ሁሉ

12= የ12ኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ሁሉ

20 ሰርተፊኬት ትምህርት መስጫ ከታወቁ ተቋሞች (ኮሌጆች) ዩኒቨርስቲዎች ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ወይም

ዲግሪ ለማስገኘት ባልታቀደ ፕሮግራም የአንድ ዓመትና ከዚያ

በላይ ትምህርት ለፈጸሙ ሁሉ፣ ፕሮግራሙን አጠናቀው ሰርተፊኬት የተቀበሉ ሁሉ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ፡፡ በዓምድ 26 ውስጥ ከሀ እስከ ቸ ከተዘረዘሩት ውጭ የተከታተሉት ትምህርት ወይም ያገኙት ሰርተፊኬት በዚህ ዓምድ በኮድ 20 ይመዘገባል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 21 | ዲፕሎም ያልጨረሱ | ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ከታወቁ ተቋም ወይም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ለማስገኘት በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም የአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን ዲፕሎም ሳላገኙ ሁሉ፡፡ |
| 22 | ዲግሪ ያልጨረሱ | ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢ.ኤ.ኤስ.ሲ) ያስገኛል ተብሎ በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርስቲ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ሳጠናቀቁ ግን ዲግሪ ሳላገኙ ሁሉ፡፡ |
| 23 | ዲፕሎም | በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ተቋም (ኮሌጅ) ዩኒቨርስቲ ወይም ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ሳገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ሳላቸው ሁሉ፡፡ |
| 24 | ዲግሪና በላይ | የመጀመሪያ ዲግሪ የማስተርስና የዶክትሬት ዲግረ ሳገኙ፣ |

95 መሠረተ ትምህርት

በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ማንበብና መፃፍ ችለው በሌላ ቦታ ትምህርት ሳልቀጠሉ ሁሉ፣

96 መደበኛ ያልሆኑ — የቄስ የቁርዓንና የመሳሰሉት ትምህርት ቤቶች በመማር

ማንበብና መፃፍ የሚችሉ (ትምህርታቸው ወደ መደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተረጎም የማይቻል)፡፡ እንደዚሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን ዕርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ እዚህ ይመደባሉ፡፡ በ ተጨማሪም በመደበኛ ት/ቤት አንደኛ ክፍል ያሳጠናቀቁ ሆነው ነገር ግን ማንበብና መፃፍ የሚችሉ በዚህ ክፍል ይካተታሉ፡፡

ትምህርትን ከመደበኛ ትምህርት ቤትና ዩኒቨርስቲ ውጭ የተከታተለ ወይም በመከታተል ላይ ያለ ማንኛውም ሰው የጨረሰውን ከፍተኛ ክፍል ለማወቅ በተቋሙ የስንት ዓመት ትምህርት ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ደረጃ እንደአጠናቀቀ እና በመደመ ር ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ነርሶች የትምህርት ቤት ከመገባታቸው በፊት በመደ በኛ ትምህርት የ8ኛ ክፍል ቢያጠናቅቁና በነርሶች ትምህርት ቤት የሦስት ዓመት የመ ‐ያ ትምህርት ቢያጠናቅቁ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል 8+3= 11 ይሆናል፡፡ በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም፣ በንግድ፣ በተግባረዕድ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን፣... ወዘተ. ትምህርት ቤቶ

ች ወይም ተቋሞች ትምህርት የተከታተሉ ወይም በመከታተል ላይ ያሉ ሁሉ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል በተመሳሳይ መንገድ መገኘት አለበት፡፡

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚገባው በተለያዩ የትምህርት ተቋሞች የተማረ ግለሰብ የጨረሰው ክፍል ተብሎ የሚመዘገበው ከጨረሰው የትምህርት ደረጃ መካከል ከፍተኛውን በመውሰድ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ነርስ በመደበኛ ትምህርት 11ኛ ክፍል አጠናቅቀው በነርሶች ተቋም ደግሞ የ3 ዓመት ትምህርት ቢጨርሱ በተጨማሪ በማታ ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ትምህርት ቢያጠናቅቁ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ሲባል በመጀመሪያ በመደበኛ ትምህርት ቤት 11ኛ እና በነርሶች ተቋም 3 ዓመት ስለተከታተሉ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል 14 /11+3/ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል በመደበኛ ትምህርት በማታ 12ኛ ክፍል ጨርሰው ትምህርታቸውን በዩኒቨርስቲ ቀጥለው የ3ኛ ዓመት ትምህርት ከአጠናቀቁ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል 15/11+1 +3/ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከ12 በላይ የሦስት ዓመት ትምህርት ስለአጠናቀቁ የተማሩት ዲግሪ ለማግኘት ባልታቀደ ፕሮግራም ከሆነ "20" ዲግሪ ለማግኘት በታቀደ ፕሮግራም ከሆነ ኮድ "21" ይሞላላቸዋል፡፡

## ዓምድ 18፡- የጋብቻ ሁኔታ፡

ይህ ዓምድ ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ የቤተሰብ አባላት ሁሉ መሞላት አለበት፡፡ ዕድሜአቸው ከአሥር ዓመት በታች ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት በየስማቸው አቅጣጫ በዓምድ 18 አንድ ሠረዝ /-/ ይሞላል፡፡ ጋብቻ ማለት አንድ ወንድና ሴት በሕጋዊ፣ በሃይማኖታዊ ወይም በባሕላዊ መንገድ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ፈጽመው እንደ ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ነው፡፡ ስለዚህ ዕድሜአቸው አስር ዓመትና በላይ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላትን የጋብቻ ሁኔታ በመጠየቅ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የጋብቻ ኮዶች በዓምድ 18 በካርድ ኮለም 33 የጋብቻ ሁኔታ የሚያመለክት ትክክለኛ ኮድ ይሞላል፡፡

1 = አግብተው የማያውቁ /ፈጽሞ ያላገባ ወይም ያላገባች/

2 = ባለትዳር /ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት በጋብቻ ላይ ያለ ወይም ያለች፣ ባልና ሚስት ባለመግባባት ምክንያት ጉዳያቸው በሽማግሌዎች በመታየት ላይ ያለ ወይም ፍርድ ቤት በቀጠሮ የሚገኙ ከሆነ ፊርማው እስከአልተቀደደ ድረስ ወይም ጋብቻው እስከአልፈረሰ ድረስ በትዳር እንደሚገኙ ይቆጠራል፡፡

3 = የተፋቱ /ከጥናቱ በፊት ባል ወይም ሚስት አግብታ ወይም አግብቶ የነበረ ነገር ግን በጥናቱ ጊዜ በሕጋዊ ወይም በባሕላዊ መንገድ የተፋታ ወይም የተፋታች/

4 = ባለቤታቸው የሞተባቸው /ባል/ሚስት ከሞተባቸው በኃላ እስከ ጥናቱ ጊዜ ያላገቡ/

<u>ዓምድ 19 - 24 - ባለፉት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት ላይ ስለደረሱ በሽታዎች</u>

በሽታ/ሕመም ማለት የአካል ወይም የአእምሮ ደህንነት መጓደል ማለት ነው:: በሌላ አነጋገር በሽታ የጤንነት መጉደል ወይም አለመሟላት ማለት ነው:: ማንኛ ውም የቤተሰብ አባል ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ለአጭር ጊዜ /አንድ ሰዓት/ እንኳ በ ሆን በሽታ ይዞት/ታሞ እንደነበረ ከገለጸ በሽታ ይዞት/ታሞ እንደነበረ ይቆጠራል:: ስለዚህ ማንኛውም የቤተሰቡ አባል ጥናቱ ከሚካሄድበት ዕለት ጀምሮ ወደኋላ በመቁ ጠር ባለፉት 14 ቀናት በሽታ የደረሰበት መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣ ታሞ ከነበረ የበሽ ታው ዓይነት፣ በሽታው ለስንት ቀን እንደቆየበት እና በበሽታው ምክንያት የዘወትር ተግባሩን አቋርጦ የሰነበተበት ቀናት ብዛት በእነኚህ 5 ዓምዶች ውስጥ ይመለከታሉ:: አንድ ሰው ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ በአንድ ጊዜ ወይም በተለያዩ ጊዜ ከአንድ በበ ለጡ በሽታዎች ሊጠቃ ስለሚችል ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እስከ ሁለት በሽታዎች ለመመዝገቢያ ቦታዎች ተሰጥቷል::

ያለፉት 14 ቀናት ሲባል ምን ያህል ወደ ኋላ መቁጠር እንዳለባቸው ወይም ከመቼ ጀምሮ መሆን እንዳለበት ለብዙ መልስ ሰጪዎች በትክክል ግልጽ ላይሆን ይችላ ል:: ስለዚህ በማያጠራጥር ሁኔታ ግልጽ እንዲሆንላቸው ጥያቄዎች በጥንቃቄና ቀላል በሆነ መንገድ መቅረብ አለባቸው:: ለምሳሌ ቤተሰቡ የሚጠናው ሰኞ ዕለት ከሆነ ከ ዚህ ዕለት በፊት ባሉት 14 ቀናት በሽታ ደርሶብዎት ወይም ታመው ነበር ወይም የ ጥናቱ ቀን ሐሙስ ከሆነም ከዚህ ዕለት በፊት በነበሩት 14 ቀናት ውስጥ በሽታ ደርሶ ብዎት ነበር ወይም የሚጠናው በሚያዝያ 8 ቀን 1990 ዓ.ም ከሆነ ከመጋቢት 24 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ትላንትና ድረስ/ከሚያዝያ 7 ቀን 1990 እስከ መጋቢ ት 24 ቀን 1990 ባሉት 14 ቀናት/ በሽታ ደርሶብዎት ነበርን ብሎ መጠየቅ ያስ ፈልጋል ጥናቱ ሚያዝያ 9 ቀን 1990 ለሚጠናላቸው ቤተሰቦች ባለፉት 14 ቀናት ማለት ከሚያዝያ 8 - ነሐሴ 22 ቀን 1990 ያለው ማለት ነው:: ይህ ማለት ያለፉ ት 14 ቀናት ለሁሉም ቤተሰብ አንድ የተወሰነ ቀን ሊሆን አይችልም::

ዓምድ 19:- ታመው ነበር /ባለፉት 14 ቀናት/?

ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ አንድ ሰው ታሞ ነበር የሚባለው በሽታው በዚህ ወቅት የጀመረው የሆነ እንደሆነ ብቻ ሳይሆን በሽታው ቀደም ብሎ የያዘው ሆኖ ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ሕመሙ ከቀጠለ ያው በዚህ ወቅት ታሞ እንደነበረ መቆጠር አለበት:: በተጨማሪ ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ለጥቂት ቀን ታመው የዳኑ አባላት መዘንጋት የለባቸውም:: ዋናው ነገር በሽታው መቼም ይጀምር ባለፉት 14 ቀናት ለተወሰኑ ሰዓቶች ወይም ቀናት ሰውየው በሕመም ላይ መኖሩ ነው:: በሽታ ሲባል ማንኛውም በሽታ መሆኑን አለመዘንጋት ነው:: በሽታው ረጂም ጊዜ የቆየ (chronic) ወይም ለአጭር ጊዜ አጥቅቶ የሚለቅ ዓይነት ሊሆን ይችላል::

ስለዚህ ማንኛውም የቤተሰብ አባል ጥናቱ ከሚደረግበት ዕለት በፊት በነበሩት 14 ቀናት ውስጥ መታመሙን ከገለጸ መልሱ "አዎን" ይሆናል:: ነገር ግን ባለፉት 14 ቀናት በሽታ ካልደረሰበት ትክክለኛ መልሱ "የለም" ነው:: ስለዚህ "አዎን" ወይም "የለም" በማለት ፈንታ ከሚከተሉት ኮዶች ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምድ 19 መጻፍ አለበት::

አዎን = 1 የለም =2

በሽታዎች ያሉባቸው አንዳንድ ሰዎች /በተለይ በሽታዎቹ የቆዩ ከሆኑ/ በሽታ ያለባቸው መሆኑን ሊዘነጉ ስለሚችሉ የቆየ፣ ከረጂም ጊዜ በፊት የጀመረ ነገር ግን ያልዳነ . ... ወዘተ. በሽታ ባለፉት 14 ቀናት አልነበረብዎትም ወይ እያሉ ሳያጣሩ "የለም" የሚለውን መልስ መቀበል አያስፈልግም:: በመልስ ሰጭዎች ሊረሱ የሚችሉ በሽታዎች ለምሳሌ ያህል አዝማ፣ የቆየ የአባለዘር በሽታ፣ እንቅርት፣ የሚጥል በሽታ፣ የቆየ ቁርጥማት፣ የአእምሮ በሽታ /እብደት/፣ የልብ ድካም፣ የሥጋ ደዌ በሽታ፣ የጉበት በሽታ፣ የኩላሊት በሽታ፣ የተጓደለ አመጋገብ፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ የስኳር በሽታ፣ ....ወዘተ የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ አንድ ሰው በዚህ ወቅት በሽታ አልደረሰብኝም ሲል ወይ የልብ ድካም ወይም የቆየ ቁርጥማት፣ ...ወዘተ. የለብዎትም፣ አልነበርዎትም፣ የለበትም፣ የለባትም እያሉ በተጨማሪ መጠየቅ ያስፈልግ ይሆናል::

ነገር ግን በአደጋ ምክንያት የደረሰ ጉዳት እንደ በሽታ እንዳይቆጠር መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ አንድ ሰው ወድቆ እጁን ስለተሰበረ በመታከም ላይ ቢሆን ጉዳት ነው እንጂ በሽታ ስላልያዘው እንደታመመ አይቆጠርም:: ስለዚህ ወድቆ እጁን ከመሰበሩ በቀር በተጨማሪ በሽታ ያልደረሰበት ከሆነ ምንም በሽታ እንዳልደረሰበት መቆጠር አለበት:: ለዚህ ሁኔታ መልሱ የለም ስለሆነ ኮድ"2" መጻፍ አለበት:: እን

ደዚሁም በሬ ወግቶት፣ አውሬ ነክሶት፣ መርዝ ወስዶ፣ ጎርፍ አንገላቶት፣...ወዘተ. አን ድ ሰው ጉዳት ቢደርስበት በሽታ እንደያዘው መቆጠር የለበትም።

<u>ዓምድ 20 እና 21 :- ለዓምድ 19 መልሱ "1" ከሆነ በሽታው ምን ነበር ወይም በሽታዎቹ ምን ምን ነበሩ?</u>

ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ በሽታ ይዞት እንደነበር ለገለጸ ወይም ለታወቀ ማን ኛውም የቤተሰብ አባል /ማለት በዓምድ 19 የሠፈረው መልስ "1" ከሆነ /የበሽታው / የበሽታዎቹ ዓይነት /ስም/ በነዚህ ዓምዶች መጻፍ አለበት። ይኸውም በሽታው አ ንድ ብቻ ከሆነ ሁለቱን ዓምዶች መጠቀም ስለማያስፈልግ የመጀመሪያው /ዓምድ 20 / ብቻ ይበቃል። በዚህ ጊዜ ሁለተኛው ዓምድ /ዓምድ 21/ በሠረዝ ይታለፋል። ስ ለዚህ ሁለቱን ዓምዶች /ዓምድ 20 እና 21/ መጠቀም የሚገባው ለአንድ ሰው ሁለ ት በሽታዎችን መመዝገብ ሲያስፈልግ ብቻ ነው። አንድ ሰው በተባለው ወቅት ከሁ ለት በበለጡ በሽታዎች ሊጠቃ ይችላል። ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥ ም መረጃዎች የሚሰበስቡት ለታማሚው ይበልጥ ከባድ/ሐይለኛ ስለሆኑት ሁለት በሽ ታዎች ብቻ መሆን አለበት።

የበሽታዎችን ዓይነት በትክክል ለመለየት ይረዳ ዘንድ ተለይተው ሊታወቁ የማ ፈልጉ በሽታዎች ስም ዝርዝር ከነ መለያ ምልክቶቻቸው (Symptoms) ከዚህ በታች ይገኛል። በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱት በሽታዎች በ8 ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለዋል ። በያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ደግሞ ጥቂት በሽታዎች ከነመለያ ምልክቶቻቸው (Sympt oms) ተዘርዝረዋል።

ስለዚህ እያንዳንዱ በሽታ የያዘውን ሰው በሽታው አንድ ብቻ ከሆነ እንዴት እንደሚያደርገውና እንደሚሰማው ወይም ሲያደረገውና ሲሰማው እንደነበረ በመጠየ ቅ በዚህ የበሽታዎች ዝርዝር ከተሰጡት ምልክቶችና ስሜቶች ጋር በማገናዘብ መጀመ ሪያ ከስምንቱ ዋና ዋና ክፍሎች በሽታው ከየትኛው ክፍል መመደብ እንዳለበት፣ በክ ፍሉ ውስጥ ደግሞ የትኛው በሽታ እንደሆነ በማጣራት የበሽታውን ስም በዓምድ 20 ውስጥ በተሰጠው ቦታ ላይ መጻፍ ነው። ባለፉት 14 ቀናት ሁለተኛ በሽታ እንደነበ ረበት ከተረጋገጠ ደግሞ ከፍ ብሎ በተገለጸው መንገድ በሽታው ምን እንደሆነ በማጣ ራት የበሽታውን ስም በዓምድ 21 ውስጥ መጻፍ ነው።

ታማሚው ሰው ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ እንደዚህ ሲያደርገኝ እንዲህ ሲሰማኝ ነበር ብሎ የሚገልጻቸው ምልክቶች የሚገናዘቡት በዝርዝር ውስጥ ከተሰጡት በሽታዎች መካከል ከአንድ ብቻ ሳይሆን የሁለት ወይም የሶስት በሽታዎችን ምልክቶች የሚያጣምሩ ከሆነ ከዝርዝሩ በተሰጡት ምልክቶች በመመራት አንዱን በሽታ ከሌላው መለየት ያስፈልጋል። ይህም ሲሆን ለታማሚው ሰው ይበልጥ ኃይለኛ በሆኑበት ሁለት በሽታዎች ላይ ብቻ ማተኮር ያስፈልጋል። ከሁለቱም ይበልጥ ከባድ የሆነው በሽታ ስምና ኮዱ በዓምድ 20 ሲመዘገብ የሁለተኛው በሽታ ስምና ኮዱ ደግሞ በዓምድ 21 ይጻፉል።

አንዳንድ ሰዎች የያዛቸውን በሽታ ሰም ይናገሩ ይሆናል። እርግጥም አንዳንድ በሽታዎች በአገሬው ተለይተው ሊታወቁ ይችሉ ይሆናሉ። ለምሳሌ የወባ በሽታን ብዙዎች በትክክል እንደሚለዩት ይገመታል። ሆኖም መልስ ሰጪዎች አንድን አባል ያጠቃ የበሽታ ስም ሲሰጡ እንዳለ ተቀበሎ መመዝገብ ፈጽሞ አይገባም። መጀመሪያ የተባለው በሽታ በዝርዝሩ ውስጥ መኖሩን ካረጋገጡ በኋላ በተጨማሪ በሽታው ታማሚውን እንዴት እንደሚያደርገውና ምን ስሜቶች እንደሚሰሙት ጠይቆ በዝርዝሩ ውስጥ ለበሽታው ከተዘረዘሩት ምልክቶችና ስሜቶች ጋር መስማማታቸውን ካረጋገጡ በኋላ መመዝገብ ይገባል። ታማሚው የተጠቀሰው ምልክቶችና ስሜቶች የተጠቀሰው በሽታ ከሚያስከትላቸው ምልክቶችና ስሜቶች ጋር ካልተስማሙ ግን በዝርዝሩ ውስጥ ምልክቶቹና ስሜቶቹ ተመሳሳይ የሆነ የሌላ በሽታ ስም መመዝገብ ያስፈልጋል። መልስ ሰጪው ምች መታኝ፣ መጋኛ መታኝ፣ ... ወዘተ ቢል እንዴት ያደርግሃል እያሉ በመጠየቅ የበሽታውን ምልክቶች አውቆ ዝርዝሩ ውስጥ ከተሰጡት ጋር በማገናዘብ መለየት ነው እንጂ እንዲሁ መተው ወይም ምች... ብሎ መጻፍ አይገባም።

<u>የጤና መታወክ ምልክቶች፣ ስሜቶችና የበሽታዎች ስሞች</u>

<u>ት ኩ ሳ ት</u>

11 ከፍተኛ እያቋረጠ የሚመለስ ትኩሳት ከማንቀጥቀጥ ብርድ ብርድ ማለት ጋርና የሰውነት ድካም፣______________________________ "<u>ወባ</u>"

12 ትኩሳትና ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሰውነት የሚጠፉ ሽፍታ ጋር፣___"<u>ኩፍኝ"</u>

13 ትኩሳት ከማቅለሽለሽና ዓይን ብጫ መሆን ጋር ቀለሙ የነጣ ሰገራ፣ መገጣጠሚያ ላይ ቁርጥማት ትውከት፣ ምግብ ማስጠላት፣ __________ "<u>የወፍ በሽታ</u>"

14 ትኩሳት ከአንገት መገተር ጋር፣ ትውከት እንዲሁም በሰውነት ላይ የሽፍታ ምልክት፣____________________ "አንገት ገትር"

15 ትኩሳት ከከባድ ራስ ምታት ጋር አንዳንድ ጊዜ ሰውነት መሳት፣ ድካም፣/ብዙውን ጊዜ በወረርሽኝ መልክ የሚዛመት/፣__________ "ተስቦ"

16 ሌላ ከላይ ያልተገለጹ የትኩሳት በሽታዎች፣ ለምሣሌ ጉድፍ ...ወዘተ "ሌላ ትኩሳት"

ሳ ል

21 ለረጅም ጊዜ /3 ወር ወይም በላይ/ የቆየ ሳል ከወፍራም አክታ/ደም የተቀላቀለበት ሊሆን ይችላል/ ከሰውነት ክብደት መቀነስ ጋር አንዳንድ ጊዜ መጠነኛ ትኩሳትና ሌሊት ማላብ፣____________________ "ሳምባ ነቀርሳ"

22 ለአጭር ጊዜ የቆየ /ከ3ወር ያነሰ/ ሳል፣ ትኩሳትና በደረት ዙሪያ ውጋትና ትንፋሽ ማጠር ጋር አክታ፣____________________ "ኒሞኒያ"

23 ኃይለኛ /አጣዳፊ/ሳል ከትኩሳትና ትክትክ ጋር ብዙውን ጊዜ ከ5 ዓመት በታች በሆኑ ልጆች የሚታይ፣____________________ "ትክትክ"

24 ሌላ ከላይ ያልተገለጹ የሳል በሽታዎችና ስሜቶች ለምሳሌ ጉንፋን፣ ትንፋሽ ማጠር፣ አዝማ፣ ውጋት ...ወዘተ________________ "ሌላ ሳል"

ተቅማጥና የሆድ በሽታ

31

የሚያጣድፍ ቀጭን ዓይነ ምድር፣ ደም የተቀላቀለበት ሊሆን ይችላል አንዳንድ ጊዜም ንፍጥ የሚመስል እዳሪ ...ወዘተ በየቀኑ ከተለመደው ሁኔታ ይበልጥ በመደጋገም ሲከሰት ነው። ____________________ "ተቅማጥ"

32 በቀን ከ3 ጊዜ የበለጠ ተቅማጥ ከትውከት ጋር ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት፣__________________ "ጋስተሮ ኢንቶራይቶስ"

33 እንደ ወስፋት፣ ኮሶ የመሳሰሉት በበሽተኛው የታዩ የሆድ ትላትሎች፣ __________________ "ጥገኛ የሆድ ትላትል"

34 ሌላ ተቅማጥና የሆድ በሽታ ምሳሌ የጨጓራ በሽታ፣ ሆድ መንፋት ...ወዘተ __________________ "ሌላ ተቅማጥና የሆድ በሽታ"

## አንገትና እራስ ላይ የሚታዩ በሽታዎች

41 በአንገት ላይ ከፊት በኩል በውጭ የሚታይ ስቃይ የሌለበት/የማያም/ እብጠት በተለይም ምራቅ፣ ውሃ፣ ምግብ ሲውጡ ወደ ላይና ታች የሚነቃነቅ፣ __________________ "እንቅርት"

42 አንዳንድ ጊዜ መግል ያለው የጆሮ መታመም /የቆየ ያለመስማት፣ ችግርን አይጨምርም፣/__________________ "የጆሮ ሕመም"

43 የዓይን ሕመም ከዓይን አር ጋር ሊሆን ይችላል፣ /የአንድ ወይም የሁለት ዓይኖች መታወርን አይጨምርም፣__________________ "የዓይን ሕመም"

44 በህጻናት ላይ የሚገኝ የጉሮሮ ህመም አንዳንድ ጊዜ በአንገት አካባቢ ከፊት በኩል ከውጭ /ከፍ ብሎ/ የሚታይ ሕመም ያለበት እብጠት፣______ "የጎሮሮ ሕመም" የመዋጥ ችግር ትውከት፣ ትኩሳት፣

45 የጥርስና የድድ ሕመም፣__________________ "የጥርስና የድድ ሕመም"

46 ሌላ የአንገትና የራስ በሽታ ምሳሌ ራስ ምታት፣ ነስር፣ ጆሮ ደግፍ ...ወዘተ __________________ "ሌላ የአንገትና የራስ በሽታ"

## የአባለዘር በሽታ

51 በሴቶች ወይም በወንዶች ላይ የሚታይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚመጡ በሽታዎች ምሳሌ ጨብጥ፣ ቂጥኝ፣ በብልት ላይ ወይም አካባቢ ቁስል፣ እብጠት....ወዘተ ____________________ "የአባለ ዘር በሽታ"

በቆዳ ላይ የሚታይ በሽታ

61 አደጋ ሳይደርስ በቆዳ ላይ የሚታዩ ቁስሎች እከክ፣ ችፌ፣ ቁስል.... ወዘተ. ____________________ "በቆዳ ላይ ቁስል"

62 "የሰጋ ደዌ" ____________________ "የስጋ ደዌ"

63 በአንድ እግር ወይም በሁለት እግሮች ወይም በብልት ፍሬዎች ላይ የቆየ በጣም ትልቅ ዕብጠት ____________________ "ዝሆኔ"

64 ሌላ በቆዳ ላይ፣ የሚታዩ በሽታዎችና ስሜቶች ለምሳሌ ለምጥ፣ አባ ሰንጋ፣ ....ወዘተ. ____________________ "ሌላ የቆዳ ላይ በሽታ"

በተለይ ነፍስ ጡሮችን፣ አራሶችንና ለአቅመ ሔዋን የደረሱ ሴቶችን ሁሉ የሚመለከቱ የጤና ችግሮች፣

71 የጤና መታወክ ያለበት እርግዝና/ለምሳሌ ከማህፀን ወይም ከብልት ደም መውጣት፣ እግር ማበጥ፣ ትኩሳት፣ ድካም፣ መገርጣት፣ ...ወዘተ. ____________________ "ውስብስብ እርግዝና"

72 ከሰባት ወር ዕርግዝና በፊት የሆነ ውርጃ፣ ____________________ "ውርጃ"

73

በወሊድ ጊዜ የጤና ችግር ለምሳሌ በወሊድ ጊዜ ከመጠን በላይ ደም መፍሰስ፣ ረጅም ጊዜ የወሰደ አድካሚ ምጥ፣ ____________________ "አስቸጋሪ ወሊድ"

74 ከወሊድ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ በወሊድ ምክንያት የጤና ችግር ለምሳሌ ትኩሳት ____________________ "የአራስ የጤና ችግር"

75 "የወር አበባ በሽታና ሌሎች የእናቶች በሽታዎች" ____________________ "የወር አበባ በሽታና ሌሎች የእናቶች በሽታዎች"

ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ በሽታዎች

81 የሰውነት መክሳት ከኃይል ማጣት ጋር የሰውነት ማበጥ፥ በደም ማነስ መገርጣት፥ የራስ ጠጉር ቀለም መለወጥ በተለይ የሕፃናት በሽታ፥________________

"የተጓደለ አመጋገብ"

82 የመንጋጋ አልከፈት ማለት ከጡንቻዎች ጋር ቁስል የነበረው ወይም ያለው ወይም በቅርብ ጊዜ ውስጥ የተወለደ/ከወር ወዲህ/ወይም በቅርብ ጊዜ የወለደች/ከወር ወዲህ/_____________________ "መንጋጋ ቆልፍ"

83 የአእምሮ በሽታ ለምሳሌ እብደት፥___________________ "እብደት"

84 ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ የጤና በሽታዎች ለምሳሌ አጠቃላይ ድካም፥ ልብ ድካም፥ ቁርጥማት፥ የኩላሊት በሽታ፥ የደም ብዛት፥ የደም ማነስ፥ የስኳር በሽታ...... ወዘተ__________________ "ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ በሽታዎች"

ዓምድ 22 - 23 በሽታው /ባለፉት 14 ቀናት/ ለስንት ቀናት ቀየብዎት?

እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው ታማሚው ሰው በዓምድ 20 ውስጥ በተመዘገበው የበሽታ ዓይነት ወይም በዓምድ 20 እና 21 በተመዘገቡት በሽታዎችና ባልተመዘገቡም በሽታዎች ጭምር ሲሆን በጠቅላላው በበሽታ ምክንያት ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ለስንት ቀናት እንደተጠቃ/ስንት ቀን እንደታመመ ነው:: ይኸውም የሚሰፍረው የቀኖች ብዛት መሆኑ ነው:: አንድ ሰው ሲታመም የግዴታ መተኛት ወይም ቤት ውስጥ መዋል አለበት ማለት ያለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: በተለይ አንዳንድ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ወይም የሚቆዩ (Chronic) በሽታዎች ያሉዋቸው ሰዎች ከሞላ ጎደል በደንብ ለረጂም ጊዜ በሥራ ላይ ተሰማርተው ሊቆዩ ይችላሉ:: በሽታው /በተለይ ክሮኒክ ከሆነ/ ካለፉት 14 ቀናት መጀመሪያ በፊት የጀመረ ወይም የተነሳ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን እዚህ የሚፈለገው ካለፉት 14 ቀናት ታማሚው ለስንት ቀናት በበሽታ/በበሽታዎች እንደተጠቃ/ታመመ ስለሆነ የሚመዘገበው የቀናት ብዛት በምንም ዓይነት ከ14 የበለጠ ሊሆን አይችልም:: በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ለአንድ ቀን ወይም ከቀኑ ለጥቂት ሰዓቶች /ለአንድ ሰዓት እንኳ/ የታመመ ቢሆን ለአንድ ቀን እንደታመመ ተቆጥሮ በዓምድ 18 በሽታው ለአንድ ቀን እንደ ቆየበት በማሰብ "01" የሚል አኃዝ ማስፈር አስፈላጊ ነው:: እንደዚሁም ሌላ ግለሰ

ብ ለሦስት ሙሉ ቀናትና በተጨማሪም በአራተኛው ቀን ለአንድ ሰዓት የታመመ ቢሆ ን ግለሰቡ ለአራት ቀን የታመመ መሆኑን ለመግለጽ በዓምዱ መመዝገብ ያለበት "04" መሆን አለበት፡፡ ሌላ ሰው ደግሞ ባለፉት 14 ቀናት መጀመሪያ በአንድ በሽታ ምክ ንያት ለ5 ቀናት ታሞ ከዳነ በኋላ እንደገና ሌላ በሽታ ይዞት ለ7 ቀናት ቢቆይበት በ ጠቅላላው ለ12 ቀናት ስለታመመ በዚህ ዓምድ «012» ይመዘገባል፡፡ ከምሳሌዎቹ እን ደሚታየው የቀኖቹ ብዛት ከ10 በታች ከሆነ በስተግራ በኩል ""0"" በመጨመር ባለሁ ለት ዲጂት/አኃዝ/ አድርጎ መጻፍ ያስፈልጋል፡፡

<u>ዓምድ 24፡- በበሽታ ምክንያት/ባለፉት 14 ቀናት/ የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ?</u>

አንድ ሰው በማንኛውም ቀን የዘወትር ተግባር ይኖረዋል፡፡ የዘወትር ተግባር የ ሚባለው አንድ ሰው በበሽታ ወይም በሌላ ምክንያት ባይተጓጐል ኖሮ በዚያን ቀን ወ ይም በነዚያ ቀኖች በአብዛኛው የሚያከናውነው ተግባር ነው፡፡ ለምሳሌ ሥራ መሥራ ት እርሻ፥ ንግድ፥ ልብስ ስፌት፥ ማስተማር፥ ማከም... ወዘተ./ትምህርት ቤት ሄዶ መማር፥ መጫወት/ በተለይ ለሕፃናት/፣ ሽማግሌ ከሆኑ ቤተክርስቲያን ወይም መስጊ ድ ሄዶ መጸለይ..... ወዘተ. አንድን ሰው በሽታ ይዞት ከበረታበት የዘወትር ተግባሩን ከመፈጸም ሊያግደው ይችላል፡፡

የዘወትር ተግባሩን ከማከናወን የሚታገደውም በበሽታ ምክንያት በመተኛቱ ወ ይም ቤት ውስጥ በመዋሉ ወይም ዓቅምና ብርታት ስላነሰው ወይም ሕክምና በመውሰ ድ ላይ በመሆኑ ነው፡፡

እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚመዘገበው እያንዳንዱ የታመመ ሰው በበሽታ ምክንያ ት ካለፉት 14 ቀናት የዘወትር ተግባሩን ለማከናወን ያልቻለባቸውን ቀናት ብዛት ነ ው፡፡ እዚህም ሊሠፍር የሚችለው <u>የቀናት ብዛት በምንም ዓይነት ከ14 መብለጥ የለበ ትም</u>፡፡ ያቋረጡትን የዘወትር ተግባር በአንደኛና በሁለተኛ በሽታ የተመዘገቡትንና ሌ ሎች ተጨማሪ በሽታዎችንም (ያልተመዘገቡ ካሉ) ይጨምራል፡፡

<u>ዓምድ 25 - 26፡- በአደጋዎች ምክንያት ባለፉት 14 ቀናት ስለደረሱ ጉዳቶች፣</u>

ጥናቱ ከሚሄድበት ዕለት በፊት የነበሩትን ቀኖች ወደ ኋላ በመቁጠር ባለፉት 14 ቀናት ማንኛውም የቤተሰብ አባል በሆነ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ወይም አለመሆኑ፥ በአደጋ ምክንያት የደረሰው ጉዳት በሰውየው ላይ የቆየበት ቀና ት ብዛት፥ በአደጋ ምክንያት በደረሰው ጉዳት ምክንያት የዘወትር ተግባሩን አቋርጦ የ

ሰነበተበት ቀናት ብዛት በተከታታይ ባሉት በሦስት ዓምዶች ውስጥ ይመዘገባሉ። አ ሁንም በዓምድ 19 እስከ 24 እንደተደረገው ሁሉ ያለፉት 14 ቀናት ሲባል ምን ማለ ት እንደሆነ ለመልስ ሰጪዎች በደንብ ግልጽ እንዲሆንላቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ሕፃናትን በሚመለከት መልሱን ከእናት፥ አባት ወይም ሌላ ኃላፊነት ካለው አባል ማ ግኘት ይገባል።

ዓምድ 25:- በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶብዎታል /ማለት ባለፉት 14 ቀናት/?

እዚህ ላይ በሽታዎች በአደጋዎች ምክንያት እንደደረሱ ጉዳቶች እንዳይቆጠሩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ጉዳቶች የሚባሉት በሆኑ አደጋዎች በጥል ወይም በሌ ላ ምክንያት የደረሱ ለምሳሌ:- በድንጋይ መፈንከት፥ ወድቆ መሰበር፥ በጩቤ መቀደ ድ/መወጋት መርዝ መውሰድ.... ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው እንጂ በሽታዎች /ምሳሌ ወባ፥ ኩፍኝ፥.....ወዘተ./ በቂ ምግብ አለማግኘት፥ በሥራ ብዛት መድከምና የመሳሰ ሉትን ሌሎች ችግሮች የማያጠቃልል መሆኑ ለመልስ ሰጪዎች ግልጽ እንዲሆንላቸው ማድረግ ያስፈልጋል።

አንድ ሰው በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል የሚባለውም በጉዳቱ ምክንያ ት ቢያንስ ቢያንስ ለአንድ ሙሉ ቀን የዘወትር ተግባሩን ለማከናወን ካልቻለ፥ አደጋ ው ባደረሰው ጉዳት ምክንያት ሕክምና ያደረገ፥ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ሕክምና አ ስፈልጎት ያጣን ግለሰብ ያጠቃልላል። ስለዚህ ማንኛውም የቤተሰቡ አባል ጥናቱ ከማ ደረግበት ዕለት በፊት በነበሩት 14 ቀናት ጉዳት ደርሶበት ከነበረ መልሱ "አዎን" ይ ሆናል፥ ጉዳት ካልደረሰበት ግን መልሱ "የለም" ነው። ግን "አዎን" ወይም "የለም" በ ማለት ፈንታ እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች መሰረት ነ ው።

አዎን=1 የለም=2

ባለፉት 14 ቀኖች ውስጥ አንድ ሰው ጉዳት ደርሶበት ነበር ሲባል በሆነ አደጋ ምክንያት ጉዳቱ በዚሁ ወቀት የጀመረ የሆነ እንደሆነ ብቻ ሳይሆን ቀደም ብሎ የጀ መረ ጉዳት ቢሆንም ባለፉት 14 ቀናት ውስጥም ሕመም ማድረሱን ከቀጠለ ያው ሰ ውየው በወቅቱ ጉዳት ላይ እንደነበረ ይቆጠራል።

ዓምድ 26:- አደጋ ደርሶብዎት ከተጉዱ ጉዳቱ ለስንት ቀናት ቆየብዎት

አንድ ሰው በአደጋ ምክንያት አንድ ዓይነት ጉዳት ብቻ ከደረሰበት ካለፉት 14 ቀናት ውስጥ ከደረሰበት ጉዳት ሳይድን የቆየበት ቀናት ብዛት በዚህ ዓምድ ይመዘገባል፡፡ ባለፉት 14 ቀናት ግለሰቡ ከአንድ በበለጡ ጉዳቶች፥ ከተጠቃ ደግሞ እያንዳንዱ ጉዳት የቆየበት ጊዜ ተደምሮ የቀኑ ብዛት በዓምዱ ይመዘገባል፡፡ ነገር ግን ከአንድ የበለጡ ጉዳቶች በአንድ ጊዜ ደርሰውበት ለሆነ ቀናት አንድ ላይ ቢቆዩ አንድ ጉዳት እንደደረሰበት ተቆጥሮ የቀኑ ብዛት ይመዘገባል፡፡ ሆኖም አንድ ጉዳት ለብቻው ሦስት ቀናት፥ ሌላው ጉዳት ደግሞ ለብቻው 5 ቀናት፥ ሦስተኛው ጉዳት ደግሞ ለብቻው ለአንድ ቀን ቢቆይበት በአጠቃላይ ሦስት ጉዳቶች በአንድነት ለዘጠኝ ቀናት የቆየበት መሆኑ በዓምድ መመዝገብ አለበት፡፡ ይኸውም እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው ቁጥር ባለ ሁለት ዲጂት /አኃዝ/ መሆን ስላለበት ቁጥሩ ከ 10 ያነሰ ስለሆነ በስተግራ በኩል "0" በመጨመር ባለሁለት ዲጂት አድርጎ "09" መጻፍ አለበት፡፡ እዚህም ላይ ማስታወስ የሚገባን በዓምዱ ውስጥ የሚመዘገበው የቀኖች ብዛት <u>ከ14 መብለጥ የለበትም</u>፡፡

<u>ዓምድ 27፡- አደጋ ደርሶብዎት ከተጎዱ በጉዳቱ ምክንያት የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋርጡ</u>

"የዘወትር ተግባር" የሚለው ትርጉም ቀደም ሲል በመረጃ ሰብሳቢው መመሪያ በዓምድ 22 ሥር ተሰጥቷል፡፡ እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው እያንዳንዱ በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በጉዳት ወይም በጉዳቶቹ ምክንያት ካለፉት 14 ቀናት ውስጥ የዘወትር ተግባሩን ሊያከናውንባቸው ያልቻለባቸውን ቀናት ብዛት በመደመር ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበት በጉዳቱ ምክንያት መደበኛ ተግባሩን ለማከናወን ባለመቻሉ ለሁለት ቀናት ቢያቋርጥ፥ በሌላ ጉዳት የተነሳ ደግሞ ለሌላ ስድስት ቀናት ተግባሩን ቢያቋርጥ፥ እንደዚህም በሦስተኛው ጉዳት ምክንያት ለሌላ አራት ቀኖች ተግባሩን ቢያቋርጥ በአንድ ላይ በሶስት ጉዳቶች የተነሳ ይህ ግለሰብ መደበኛ ተግባሩን ለ12 ቀናት ማቋረጡ በዓምዱ ይገለጻል፡፡ ይህም ዓምድ ሲሞላ መገንዘብ የሚገባን የሚመዘገበው የቀናት ብዛት ከ14 መብለጥ የሌለበት መሆኑን ነው፡፡ እንደዚሁም የሚመዘገበው ቁጥር ከ10 ያነሰ ከሆነ በስተግራ በኩል "0" በመጨመር ባለሁለት ዲጂት /አኃዝ/ አድርጎ መጻፍ ያስፈልጋል፡፡

<u>ዓምድ 28 - 37፡- ባለፉት 12 ወራት በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶቦዎታል? ከደረሰብዎት ጉዳት ለመፈወስ የሕክምና ዕርዳታ አገኙ? የሕክምና ዕርዳታ ካገኙ ከሚከተሉት ከየትኞቹ የሕክምና ምንጮች ዕርዳታ አገኙ?</u>

በለፉት 12 ወራት ውስጥ በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ለመዳን ሲሉ ያደረጉዋቸው ጥረቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች በእነኚህ ዓምዶች ውስጥ ይሰፍራሉ:: መጀመሪያ ሰውየው ለመዳን ሲል ከሆስፒታል፥ ጤና ጣቢያ ፥ ክሊኒክ፥ ከቀበሌ ጤና ተጠሪ፥ ከመድኃኒት ቤት ...ወዘተ. የሕክምና ዕርዳታ ማግኘቱን የሚመለከት መረጃ ይሰበሰባል:: ከዚያም የሕክምና እርዳታ ለማግኘት መሞከሩ የተረጋገጠ ከሆነ /ለዓምድ 28 መልሱ "1" ከሆነ/ እርዳታውን ከየት ለማግኘት እንደሞከረ ከዓምድ 30-38 ካሉት በየትኞቹ ዕርዳታ እንዳገኘ አንድ በአንድ በመጠየቅ ትክክለኛው ኮድ በየዓምዱ በተሰጠው ካርድ ኮለም ይመዘገባል::

አንድ ሰው ባለፉት 12 ወራት በበሽታና በአደጋ ምክንያት ከደረሰበት ጉዳት ለመዳን ከአንድ በላይ ከሆነ የሕክምና አገልግሎት ምንጮች የሕክምና ዕርዳታ ሊያገኝ ይችላል::

<u>ዓምድ 28 ባለፉት 12 ወራት በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶብዎታል?</u>

ማንኛውም የቤተሰብ አባል ባለፉት 12 ወራት መታመሙ ወይም በአደጋ ምክንያት መጎዳቱ በቅድሚያ በመጠየቅና በማጣራት በትክክል መረጋገጥ አለበት:: በመጀመሪያ ለመልስ ሰጪዎች ባለፉት 12 ወራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ማስረዳት ተገቢ ነው:: ይህም ማለት ባለፉት 12 ወራት የምንለው ጥናቱ ከሚካሄድበት ቀን በፊት የነበሩትን 12 ወሮች መሆኑን ማስረዳትና ይህም በዓምድ 19-22 እና በዓምድ 25-27 የተጠቀሰውን ያለፉት 14 ቀናትን እንደሚያጠቃልል ማስገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው:: ባለፉት 12 ወራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለቤተሰቡ በትክክል ከተገለጸ በኋላ ማንኛውም የቤተሰቡ መደበኛ አባል በተጠቀሰው ወቅት ታመው ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደረሰባቸው እንደነበረ ተጠይቆ አባሉ ባለፉት 12 ወራት ታመው ወይም ጉዳት ደርሶባቸው ከሆነ ኮድ "1" አልታመሙ ወይም ጉዳት ያልደረሰባቸው ከሆነ ኮድ "2" በካርድ ኮለም 50 ይመዘገባል::

<u>ዓምድ 29:- ለዓምድ 28 መልሱ "አዎን" ከሆነየሕክምና ዕርዳታ አገኙ?</u>

ማንኛውም የቤተሰቡ መደበኛ አባል ከተጠቀሰው ወቅት /ባለፉት 12 ወራት/ ውስጥ ከማንኛውም ቦታ ከሕመሙ ወይም በአደጋ ምክንያት ከደረሰበት ጉዳት ለመፈወስ የሕክምና ዕርዳታ ካገኘ መልሱ "አዎን" ካላገኘ ደግሞ "የለም" ስለሆነ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ተጠይቆ ተስማሚውን ኮድ መጻፍ ነው::

1=አዎን 2=የለም

እዚህ ላይ የሕክምና ዕርዳታ አግኝተዋል? ብሎ መጠይቅ በቂ አይሆንም:: ከሐኪም ቤት ወይም ከጤና ጣቢያ ወይም ከክሊኒክ የሕክምና ዕርዳታ አገኘ? ከዚያም መልሱ "የለም" ከሆነ ከቀበሌ ጤና ተጠሪስ? ከመድኃኒት ቤትስ? ከባሕላዊ አካሚስ/ወጌሻ፣ ቀጠል በጣሽ፣ ....ወዘተ/? አካሚ ካልሆነ ሰውስ ተብሎ ተጠይቆ ለዚህ ሁሉ መልሱ "የለም" ከሆነ ራስዎን አከሙ? ወይስ በሌላ ሁኔታ የሕክምና ዕርዳታ አገኙ? በማለት ተጠይቆ በመጨረሻም ለዚህ ሁሉ መልሱ "የለም" ከሆነ "ከአዋቂ " የሕክምና ዕርዳታ አገኙ .... እያሉ በመጠየቅ ማጣራት ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 30:- ለዓምድ 29 መልሱ "አዎን" ከሆነ፣ ከሆስፒታል የሕክምና ዕርዳታ /ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ/ አገኙ?</u>

ለዓምድ 29 መልሱ "አዎን" ሆኖ ግለሰቡ/ቧ ከሆስፒታል የህክምና ዕርዳታ ካገኙ መልሱ "አዎን" ካላገኙ ደግሞ "የለም" ስለሆነ ይህንኑ ጠይቆ በማጣራት ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ተስማሚው ኮድ በዚህ ዓምድ ማለትም በካርድ ኮለም 52 ይመዘገባል::

1 = አዎን 2 = የለም

<u>ዓምድ 31:- ለዓምድ 29 መልሱ "አዎን" ከሆነ ከክሊኒክ የሕክምና ዕርዳታ አገኙ?</u>

ባለፉት 12 ወራት ታመው ወይም አደጋ ደርሶባቸው የሕክምና እርዳታውን ያገኙ ከክሊኒክ መሆኑ ተጠይቆ መልሱ "አዎን" ከሆነ ኮድ "1" የለም ከሆነ ኮድ "2" በካርድ ኮለም 53 ይመዘገባል::

<u>ዓምድ 32:- ለዓምድ 29 አልሱ "አዎን" ከሆነ፣ ከጤና ጣቢያ የሕክምና እርዳታ አገኙ?</u>

ለዓምድ 29 መልሱ "አዎን" ሆኖ ግለሰቡ/ቧ ከጤና ጣቢያ የህክምና እርዳታ ካገኙ መልሱ "አዎን" ካላገኙ ደግሞ "የለም" ስለሆነ ይህንኑ ጠይቆ በማጣራት ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ተስማሚውን ኮድ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለም 54 ይመዘገባል ::

1 = አዎን 2 = የለም_

<u>ዓምድ 33:- ለዓምድ 29 መልሱ "አዎን" ከሆነ ከቀበሌ ጤና ተጠሪ የሕክምና</u>

እርዳታ /ባለፉት 12 ወራት/ አገኙ?

በዓምድ 29 መልሱ አዎን /"1"/ ሆኖ ሰውየው ከቀበሌ ጤና ተጠሪ ባለፉት 12 ወራት ቀናት ውስጥ የሕክምና ዕርዳታ ካገኘ በካርድ ኮለም 55 ኮድ "1" ነገር ግ ን እርዳታውን ያገኘው ከቀበሌ ጤና ተጠሪ ካልሆነ ኮድ "2" ይመዘገባል።

ዓምድ 34፡- በዓምድ 29 መልሱ "አዎን" ከሆነ ከመድኃኒት ቤት /ከፋርማሲ/ የሕክምና ዕርዳታ አገኙ?

ግለሰቡ ባለፉት 12 ወራት ታሞ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበት ለ መፈወስ እርዳታ ማግኘቱን በዓምድ 29 ከገለጸ ከመድኃኒት ቤት ወይም ከፋርማሲ የ ሕክምና ዕርዳታ ማግኘቱን ጠይቆ መልሱ "አዎን" ከሆነ ኮድ "1" "የለም" ከሆነ ኮድ "2" በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለም 56 ይመዘገባል።

ዓምድ 35፡- በዓምድ 29 መልሱ "አዎን" ከሆነ ከበሕላዊ አካሚ የሕክምና ዕርዳታ አገኙ /ባለፉት 12 ወራት ውስጥ/?

ባሕላዊ አካሚ የሚባሉት እንደ ቅጠል በጣሽ፣ መድኃኒት በግሉ ጨማቂ ወይ ም ቀማሚ፣ ወጌሻ፣ አዋቂ፣ ...ወዘተ. የመሳሰሉት ችሎታቸውን ያገኙት በዘመናዊ በተ መሰረተ ትምህርትና ሥልጠና ሳይሆን በራሳቸው ልምምድ ከማድረግና ከባሕል ሕክም ና አዋቂዎች ያገኙት ዕውቀት የሆነ እንደሆነ ነው። በጠበል መጠቀምም እንደዚሁ ከባሕላዊ አካሚ የሕክምና ዕርዳታ እንደማግኘት ይቆጠራል። ከአዋቂ የሕክምና እር ዳታ አግኝተዋል ወይ ብሎ ከመጠየቅ በሚቻል መጠን መቆጠብ ያስፈልጋል። በመጨ ረሻ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሌሎች ጥያቄዎች ተጠይቀው ካለቁ በኋላ ብቻ ከአዋቂ የሕክምና ዕርዳታ ማግኘታቸውን መጠየቅ ያስፈልጋል።

ስለዚህ በዓምድ 29 መልሱ አዎን /"1"/ ሆኖ ሰውየው ከባሕላዊ አካሚ ባለፉ ት 12 ወራት ውስጥ የሕክምና እርዳታ ያገኘ ከሆነ ኮድ "1" ካላገኘ ኮድ "2" በካርድ ኮለም 57 ይመዘገባል።

ዓምድ 36:- በዓምድ 29 መልሱ "አዎን ከሆነ አካሚ ካልሆኑ ሰዎች የሕክምና እርዳታ አገኙ? /ባለፉት 12 ወራት/

ባለፉት 12 ወራት ታመው ወይም አደጋ ደርሶባቸው የሕክምና ዕርዳታ ላገኙ /በዓምድ 29 ኮድ "1" ለተሞላላቸው/ ያገኙት የሕክምና እርዳታ አካሚ ካልሆኑ ሰ ዎች መሆኑ ተጠይቆ ትክክለኛው ኮድ በካርድ ኮለም 58 ይመዘገባል:: አካሚ ያልሆነ - ሰዎች የተባሉት በቂ ዕውቀት ወይም ልምድ ኖሮአቸው ሳይሆን የሚያውቁት ሰው በችግር ላይ ስለሆነ በሰሙትና እናውቀዋለን በሚሉት መድኃኒት ለጊዜውም ቢሆን የ ሚረዱ ሰዎች ናቸው::

ዓምድ 37:- ለዓምድ 29 መልሱ "አዎን" ከሆነ ራስዎን አከሙ? /ባለፉት 12 ወራት/

በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በቂ የህክምና ዕውቀ ትና ልምድ ሳይኖረው ቀደም ሲል በሰማው መሠረት ያድነኛል ብሎ ያመነውን መድ ኃኒት ገዝቶ ቅጠል በጥሶ፣ ሥር ነቅሎ፣ ወይም ቀምሞ...ወዘተ ማንም ሳያዝለት የሚወ ሰድበት ጊዜም ሊኖር ይችላል:: ስለዚህ በዓምድ 29 መልሱ አዎን /"1"/ ሆኖ ባለፉ ት 12 ወራት ውሰጥ ሰውየው ራሱን በራሱ ካከመ በዓምዱ መልሱ "አዎን"፣ ካላከመ ደግሞ "የለም" ስለሆነ ይህንኑ በደንብ ጠይቆ በማጣራት ቀጥሎ በተመለከተው መሠረ ት ተስማሚውን ኮድ በዓምድ 37 ማለት በካርድ ኮለም 59 ይጻፉል::

1 = አዎን 2 = የለም

ዓምድ 38:- በዓምድ 29 መልሱ "አዎን" ከሆነ ከሌላ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት የሕክምና አገልግሎት መስጫ ግልጋሎቶች ሌላ የሕክምና ዕርዳታ አገኙ? /ባለፉት 12 ወራት/

በዓምድ 29 መልሱ አዎን /"1"/ ሆኖ ሰውዬው ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በ ሕመም ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው በመፈወስ በዓምድ 30 እስከ 37 ከተጠቀሱት የሕክምና ዕርዳታ ዘዴዎች በተለዩ ሁኔታዎች የሕክምና ዕርዳታ ካገኙ በ ዓምዱ መልሱ "አዎን" ካላገኙ ደገሞ "የለም" ነው:: ከ"መርፌ ወጊ" ባለፉት 12 ወራ ት ታማሚው ወይም ተጎጂው የሕክምና ዕርዳታ ቢያገኝ ይህ ግለሰብ "ከሌላ" የሕክም ና ዕርዳታ እንዳገኘ ይቆጠራል:: ይህንኑ የመሳሰሉ ሃሳቦችን በማስረዳትና አጣርቶ በ መጠየቅ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ትክክለኛውን ኮድ በዓምድ 38 በካርድ ኮለም 60 ይመዘገባል::

1 = አዎን 2 = የለም

<u>ዓምድ 39:- በዓምድ 29 መልሱ "የለም" ከሆነ የህክምና ዕርዳታ ያላገኙበት ምክንያት</u>

ማንኛውም የቤተሰብ አባል ባለፉት 12 ወራት መታመሙ ወይም በአደጋ ምክ ንያት መጎዳቱ ከታወቀና ምንም ዓይነት የሕክምና እርዳታ አለማግኘቱ ከተረጋገጠ / ለዓምድ 29 መልሱ የለም "2" ከሆነ/ የሕክምና ዕርዳታ ያላገኘበት ምክንያት መታወ ቅ ስላለበት የሕክምና እርዳታ ያላገኘበትን ምክንያት በመጠየቅ በዓምዱ ግርጌ ከተሰ ጡት ምክንያቶች ትክክለኛውን ኮድ በመምረጥ በዚህ ዓምድ ማለት በካርድ ኮለም 61 ውስጥ ይመዘገባል፡፡ ሊኖሩ የሚችሉ ምክንያቶች ከነኮዶቻቸው ቀጥሎ ተዘርዝረዋል፡ ፡

1 = የሕክምና አገልግሎት መስጫ ቦታ በጣም ስለራቀኝ
2 = በቂ ገንዘብ ስለሌለኝ
3 = ይጠቅማል ብዬ ስላላመንኩ
4 = ጉዳቱ/ህመሙ ይተወኛል በማለት
5 = ለህክምና ወረፋ ስለማይደርሰኝ
6 = የሚያስፈልገውን መድኃኒት አገኛለሁ ብዬ ስለማልገምት
7 = ሌላ

መልስ ሰጭዎች ምክንያት ከመስጠት ከተቆጠቡ እነዚህን ምክንያቶች አንድ በአንድ በ መዘርዘር ከመልስ ሰጭው በማንበብ የተገኘውን ትክክለኛ ምክንያት በዓምዱ መመዝገ ብ ያስፈልጋል፡፡

<u>ዓምድ 40:- ከሆስፒታል፣ ከክሊኒክ፣ ከጤና ጣቢያ፣ ከቀበሌ ጤና ተጠሪ፣ ከመድኃኒት ቤት ሕክምና ካላገኙ ያላገኙበት ምክንያት</u>

በዓምድ 30 - 38 ዘጠኝ ዓይነት የሕክምና ዕርዳታ የመስጫ መገልገያዎች ተዘ ርዝረዋል፡፡ ስለሆነም ማንም ሕመም ወይም ጉዳት የደረሰበት ሰው ከእነዚህ ቢያንስ ከአንዱ የሕክምና ዕርዳታ ሊያገኝ ይችላል፡፡ ማንም በአለፉት 12 ወሮች የሕክምና ዕ ርዳታ ማግኘቱ የተረጋገጠለት ሰው ሕክምናውን ያገኘው ከሆስፒታል፣ ከጤና ጣቢያ፣ ከክሊኒክ፣ ከቀበሌ ጤና ተጠሪ ወይም ከመድሐኒት ቤት ሳይሆን ከሌሎች የሕክምና መስጫ ዓይነቶች ከሆነ ለምን በአንዱም ዘመናዊ የሕክምና መስጫ እንዳልተጠቀመ ጠ ይቆ በማጣራት እግርጌ ከተዘረዘሩት ስምንት አማራጭ ምክንያቶች የትክክለኛው የአን ዱ ምክንያት ኮድ በዓምድ 40 ማለት በካርድ ኮለም 62 ውስጥ ይመዘገባል፡፡ ምክንያ

ቶች ከአንድ በላይ ከሆኑ የአንዱ ዋነኛ ምክንያት ብቻ ይወሰዳል፡፡ አማራጭ ምክንያ ቶች ከነኮዶቻቸው ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

1 = አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ በጣም ስለራቀ

2 = በቂ ገንዘብ ስለሌለኝ

3 ባህላዊ መድኃኒት ስለወሰድኩ

4 = ይጠቅመኛል ብዬ ስላላመንኩ

5 = ይተወኛል በማለት

6 = ወረፋ ስለማይደርሰኝ

7 = የሚያስፈልገውን መድኃኒት አገኛለሁ ብዬ ስለማልገምት

8 = ሌላ

<u>ዓምድ 41 እና 46፡- ዕድሜአቸው 15 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ሴቶች ብቻ</u>

ዕድሜአቸው 15 ዓመት ወይም በላይ የሆኑ ሴቶች የቤተሰብ አባላት ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ መውለዳቸው ወይም አለመውለዳቸውና ልጅ ወልደው ከሆነ ደግሞ በመጨረሻ የተወለደውን ልጅ በሚመለከት የት እንደወለዱና ማን እንዳዋለዳቸው፣ በ መጨረሻ እርግዝና ጊዜ ዘመናዊ የሕክምና ዕርዳታ ማግኘት አለማግኘታቸው፣ ለእርጉ ዞች የሚሰጥ ክትባት /የቴታነስ ቶክሶይድ - ቲ.ቲ /T.T./ መከተባቸው ወይም አለመ ከተባቸውን እና በእርግዝናቸውና በእመጫትነታቸው ወቅት ተጨማሪ ምግብ ማግኘት አለማግኘታቸውን የሚመለከቱ መረጃዎች በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ ይሰበሰባሉ፡፡

እነዚህ ዓምዶች በሚሞሉበትም ጊዜ ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ ወልደው ከሆነ የመጨረሻውን ልጅ/የመጨረሻውን እርግዝና/ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በዚህም ጊ ዜ እርግዝናውን በሚመለከት ዘመናዊ የሕክምና ዕርዳታ ማግኘት ምን ማለት እንደሆ ነ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የመጨረሻው ልጅ /የመጨረሻው እርግዝና/ የተባለው ሴ ትየዋ ባለፉት 2 ዓመታት ከአንድ ጊዜ በላይ ልጅ ሊወልዱ ስለሚችሉና መረጃ መሰብ ሰብ የተፈለገው ደግሞ በስተመጨረሻ ስለተወለደው ልጅ በመሆኑ ነው፡፡ ባለፉት 2 ዓመታት ግለሰቧ አንድ ጊዜ ብቻ ከወለዱ የሚሰበሰበው መረጃ ይህን ልደት በሚመለ ከት ይሆናል፡፡ ሆኖም ባለፉት 2 ዓመታት ምንም ልጅ ካልወለዱ ወይም ሳይወልዱ ገ ና አሁን እርጉዝ ከሆኑ በዓምድ 41 መልሱ የለም በመሆኑ ከዓምድ 42-46 ምንም አ ይመዘገበም፡፡

የመጨረሻውን እርግዝና በሚመለከት ዘመናዊ የሕክምና እርዳታ አገኘ ማለ ት ደግሞ ግለሰቧ በመጨረሻው የወለዱትን ልጅ አርግዛው በነበረበት ወቅት ለክትባት ወይም ለመውለድ ወይም ከእርግዝናው ወይም ከወሊዱ ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ ታ መው ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው ለመፈወስ ወደ ሕክምና መስጫ ድ ርጅት የሕክምና ዕርዳታ ለማግኘት የሄዱበትን ጊዜ ሳይጨምር የእርግዝናውን ሁኔታ ለማስመርመር ወይም እርግዝናውን በሚመለከት የሐኪም ምክር ለመቀበል ወይም በ ተመሳሳይ የሕክምና ዕርዳታ ያገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ዘመናዊ የሕክም ና ዕርዳታ አገኙ የሚባለውም ግለሰቧ ከሆፒታል፣ ከጤና ጣቢያ ከክሊኒክ ወይም ከቀ በሌ ጤና ተጠሪ የሕክምና ዕርዳታ ካገኙ ወይም በዘመናዊ የሕክምና ሙያ በሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች ሲረዱ ነው።

ዓምድ 41:- ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ ወልደዋል?

ዕድሜአቸው 15 ዓመት ወይም በላይ የሆኑ ሴቶች ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ ልጅ ወልደው እንደሆነ ተጠይቀው መልሱ ከዚህ በታች በተመለከቱት ኮዶች መሠረ ት እዚህ ዓምድ ውስጥ ይጻፋል።

1 = አዎን　　　　2 = የለም

ምናልባት አንዳንድ ሴቶች ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ ልጆች ወልደው ልጆቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሞቱ ወልደናል ላይሉ ስለሚችሉ ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ ል ጅ ወልደው አልሞተብዎትም ብሎ በመጠየቅ ማጣራት ያስፈልጋል።

ማሳሰቢያ:- ሴትዮዋ ያስወረዳቸው ወይም ሞቶ የወለዱት ልጅ እንደ ልጅ መውለ ድ አይቆጠርም። ነገር ግን በሕይወት ተወልዶ/ተወልዳ ከሞተ/ከሞተች እንደ ወለዱ ይቆጠራል። "በሕይወት ተወለደ" ማለት አንድ ፅንስ በማህፀን የቆየበት ወራት ከግ ምት ውስጭ ሳይገባ ከእናቱ ማህፀን በሚወጣበት ወቀት የሚተነፍስ ከሆነ ወይም እት ብቱ ከመቆረጡ በፊት ወይም ከተቆረጠ በኋላ ሌላ ዓይነት በሕይወት የመኖር ምልክት ካሳየ ለምሳሌ የልብ ትርታ፣ የእትብት ትርታ፣ የጡንቻዎች እንቅስቃሴ በሕይወት የ ተወለደ ይባላል። እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው የሕይወት ምልክት አሳይቶ ወ ዲያውኑ ቢሞት እንኳ በሕይወት እንደተወለደ መቆጠሩንና የእርግዝና ወቅት መርዘ ም ሆነ ማጠር ከግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱን ነው። የማደጎ ልጆች ወይም ያሳደጓቸው ልጆች እንደወለዷቸው ልጆች አይቆጠሩም።

ዓምድ 42:- በዓምድ 41 መልስ "አዎን" ከሆነ የት ነበር የወለዱት?

ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ መውለዳቸው ለተረጋገጠላቸው ሴቶች /በዓምድ 41 መልሱ "አዎን" ከሆነ/ የመጨረሻውን ልጅ የት እንደወለዱ ጠይቆ በማጣራት መልሱ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይጻፋል:: መልሱም በዓምዱ እግርጌ ከተመለከቱት አማራጮች አንዱ ብቻ መሆን ስላለበት ትክክለኛውን መልስ መርጦ ኮዱን ብቻ በካርድ ኮለም 64 መጻፍ ያስፈልጋል:: አማራጭ የሆኑት መልሶች ከነኮዶቻቸ‍ው ቀጥሎ ተዘርዝረዋል::

1. በመኖሪያቤታቸው ወይም በሌላ ሰው መኖሪያ ቤት
2. ጤና ጣቢያ
3. ክሊኒክ
4. ሆስፒታል
5. ሌላ

ዓምድ 43:- ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ ወልደው ከሆነ፣ የመጨረሻውን ልጅ ማን ነበር ያዋለደዎት?

ባለፉት 2 ዓመት ልጅ መውለዳቸው ለተረጋገጠ ሴቶች /በዓምድ 41 መልሱ "1" ከሆነ/ ማን እንዳዋላቸው ጠይቆ በማጣራት መልሱ እዚህ ዓምድ ውስጥ መጻፍ አለበት:: መልሱም በዓምዱ እግርጌ ከተመለከቱት አማራጮች አንዱ ብቻ መሆን ስላለበት ትክክለኛውን መልስ መርጦ ኮዱን ብቻ በዚህ ዓምድ ውስጥ መጻፍ ያስፈልጋል:: አማራጭ የሆኑት መልሶች ከነኮዶቻቸው ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል:-

1. የጤና ባለሙያ /ሴትየዋ ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ድረስ በመሄደ ወይም ባለሙያው ቤታቸው ድረስ መጥተው ሲያዋልዱዋቸው፣/
2. የቀበሌ የጤና ተጠሪ፣
3. የሰለጠኑ ባሕላዊ አዋላጅ /ከቀበሌያቸው ተመርጠው የዘመናዊ አዋላጅነት ሥልጠና የተሰጣቸው/
4. ባህላዊ አዋላጅ /ያልሰለጠኑ/
5. የማዋለድ ሙያ የሌላቸው ሰው
6. ማንም አላዋለደኝም /እራሴን አዋለድኩ/

ዓምድ 44:- ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ ወልደው ከሆነ በመጨረሻው ልጅ እርግዝናዎ ወቅት ዘመናዊ የሕክምና ክትትል አግኝተዋል?

ለዓምድ 41 መልሱ "አዎን" ከሆነ ግለሰቧ የመጨረሻውን ልጅ አርግዘው በነበረ በት ወቅት ከፍ ብሎ ከተመለከቱት ዘመናዊ የሕክምና ዕርዳታ መስጫ መገለገያዎች መካከል /ከሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ክሊኒክ ወይም ቀበሌ ጤና ተጠሪ/ በአንዱ እንኳ እርግዝናውን በሚመለከት የሕክምና ዕርዳታ ማግኘታቸው ይጠየቃል። የጤና ባለ ሙያ እቤት ድረስ በመሄድ የሕክምና ዕርዳታ ከሰጡዋቸው የሕክምና ዕርዳታ እንደማ ግኘት ይቆጠራል። የሕክምና ዕርዳታ ካገኙ መልሱ "አዎን" ካላገኙ ደግሞ "የለም" ስ ለሆነ ቀጥሎ ከተመለከቱት ኮዶች ትክክለኛውን በመምረጥ በዓምዱ ማለት በካርድ ኮለ ም 66 ይመዘገባል።

1= አዎን                2= የለም

<u>ማስታወሻ:-</u> ዘመናዊ የሕክምና ክትትል አገኙ የሚባለው ግለሰቧ ከሆስፒታል ከጤና ጣቢያ፣ ከክሊኒክ ወይም ከቀበሌ ጤና ተጠሪ የሕክምና ዕርዳታ /ክትት ል/ ካገኙ ወይም በዘመናዊ የሕክምና ሙያ በሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎ ች ሲረዱ ነው።

<u>ዓምድ 45 - ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ ወልደው ከሆነ፣ በመጨረሻው ልጅ እርግዝናዎ ጊዜ የቲ.ቲ. /T.T/ ክትባት ተከትበዋል?</u>

ቲ.ቲ (TETANUS TOXOID) ለእርጉዝ ሴቶች በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ሁለት ጊዜ የሚሰጥ ክትባት ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ መውለዳቸው ለተረጋገጠላቸው ሴቶች ማለትም በዓምድ 41 መልሱ አዎን /"1"/ ለተባለላቸው ሴቶች ሁሉ በመጨረሻው ልጅ እርግ ዝና ጊዜ የተጠቀሰውን ክትባት ማግኘት አለማግኘታቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎች በዚህ ዓምድ ይሰበሰባል። በዚህ መሠረት ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ ለወለዱ ሴቶ ች በመጨረሻው እርግዝናቸው ወቅት /እረጉዝ በመሆናቸው የወሰዱት ክትባት ብቻ እንጂ ሌሎች ክትባቶችንና ሌላ ህክምናን አይጨምርም/ የቲ.ቲ. ክትባት ተደረገልዎት ? በማለት ተጠይቆ መልሱ አዎን ከሆነ "1" የለም ከሆነ "2" በዓምዱ ይመዘገባል። የክትባት ካርዱን ያሳዩ በማለት በክትባት ካርድ ማረጋገጥ ጠቃሚ ነው። የክትባት ካ ርድ ለማሳየት ላልቻሉ ሴቶችም ቢሆን በእርግዝናቸው ወቅት የእረግዝና ክትባት መ ውሰዳቸውን ለገለጹ እንደተከተቡ ይመዘገባሉ።

<u>ዓምድ 46 - ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ ከወለዱ በመጨረሻው እርግዝናዎና</u>

## እመጫትነትዎ ተጨማሪ ምግብ ተመገቡ/ይመገባሉ?

ነፍሰጡር ሴቶችና የሚያጠቡ እናቶች /እመጫቶች/ በአመጋገብ በኩል ልዩ ትኩረት ስለሚያስፈልጋቸው እነኚህ የቤተሰብ አባላት ከማንኛውም የምግብ ዓይነት ወ ይም ከአንዳንድ የምግብ ዓይነቶች ጨመርመር በማድረግ ወይም ለሌሎች የቤተሰብ አ ባላት ሳይሰጥ ለነሱ በተለይ እየተሰጣቸው የሚመገቡ መሆናቸው ወይም አለመሆናቸ ው ተጠይቆ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይመዘገባል።

አንዲት ነፍሰጡር ወይም እመጫት የሆነች ሴት ከአንድ ምግብ ዓይነት በተጨ ማሪ ትመገባለች የሚባለው ተጨማሪ ማግኘት እንደሚገባት ታምኖበት ነፍሰጡር ወይ ም ጡት የምታጠባ ባትሆን ኖሮ ከምትመገበው አሰበልጣ የተለየ ከምግቡ ስትመገብ ነ ው።

ከላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሰረት ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ መውለዳቸ ው ለተረጋገጠላቸው ሴቶች ሁሉ /በዓምድ 41 መልሱ "አዎን" ለተባለላቸው ሴት የበ ተሰብ አባላት ሁሉ/ በመጨረሻው እርግዝናቸውና በመጨረሻ እመጫትነታቸው /ጡ ት በሚያጠቡበት ወቅት/ ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ የምግብ ዓይነቶች በተጨ ማሪ የተመገቡ ወይም የሚመገቡ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ትክክለኛ መል ሶችን ለማግኘት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን አቅርቦ በማጣራት ትክክለኛውን መልስ የሚ ያሳይ ኮድ ማስገባት ነው።

በተጨማሪም አንዳንድ ሴቶች በእርግዝናቸው ወቅት ተጨማሪ ምግብ ወስደው በእመጫትነታቸው /ጡት በሚያጠቡበት ወቅት/ ግን ላይመገቡ ይችላሉ። እንደዚ ሁም በእርግዝናቸው ወቅት ተጨማሪ ምግብ ሳይመገቡ በእመጫትነታቸው/ጡት በሚ ያጠቡበት ወቅት/ ግን ሊመገቡ ይችላሉ። እነዚህን ሁኔታዎች መልሱን ከመመዝገብ በፊት ጠይቆ በማጣራት ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች አማካኝነት ትክክለኛው ሁኔታ በዓምዱ ይጻፉል፦

0 = በእርግዝናም በእመጫትነትም ወቅትበተጨማሪ ላልተመገቡ

1 = በእርግዝናቸው ወቅት ብቻ በተጨማሪ ለተመገቡ

2 = በእመጫትነታቸው ወቅት ብቻ በተጨማሪ ለተመገቡ

3 = በእርግዝናቸውና በእመጫትነታቸው ወቅት በተጨማሪ ለተመገቡ

## ክፍል 3:- የሕፃናት ክብደትና ቁመት ልክቶች፣ የአመጋገብና የክትባት ሁኔታ

### ዓምድ 47:- የሕፃኑ ተራ ቁጥር (ከክፍል 2 ዓምድ 11 የሚወራረስ)

በዚህ ዓምድ የሚመዘገበው በክፍል 2 ዓምድ 11 ለእያንዳንዱ መደበኛ አባል ከተሰጠው ተራ ቁጥር መካከል ዕድሜያቸው አምስት ዓመት በታች ላሉት ህፃናት ብ ቻ (ከጤናና አመጋገብ ጥናት መጠይቅ ክፍል 2 ዓምድ 14 ዕድሜውን በማየት) የህፃ ኑን ተራ ቁጥር ከዓምድ 11 በቀጥታ በማስተላለፍ ነው:: ሕፃናት ሲመዘገቡ ተከታታ ይ ባለው መንገድ ላይሆን ስለሚችል ወደዚህ ዓምድ ሲተላለፍም ቀድሞ የተመዘገበው ተራ ቁጥር ምንም ዓይነት ማስተካከያ ሳይደረግበት እንዳለ ነው::

ምሣሌ:- በክፍል 2 ዓምድ 11 ላይ ለሕፃኑ የተሰጠው ተራ ቁጥር "05" ቢሆን በክፍል 3 ዓምድ 47 ለሕፃኑ የሚሰጠው ተራ ቁጥር "05" ይሆናል ማለት ነው::

### ዓምድ 48:- የሕፃኑ ስም፣

ይህ ዓምድ በክፍል 3 ዓምድ 47 ተራ ቁጥሩ ለተላለፈለት ሕፃን ሙሉ ስም የ ሚመዘገብበት ዓምድ ነው:: ለተጨማሪ ማብራሪያ ክፍል 1 ዓምድ 9 የተሰጠውን ማ ስታወሻ ይመልከቱ::

### ዓምድ 49:- የሕፃኑ ወላጅ እናት ተራ ቁጥር፣

በዓምድ 49 የተጠቀሰው ሕፃን ወላጅ እናት ተራ ቁጥር የሚገኘው ከክፍል 2 ዓምድ 11 ከተዘረዘሩት የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥሮች መካከል ጠይቆ በመ ምረጥ ይሆናል:: የሕፃኑ ወላጅ እናት ተራ ቁጥር በዚህ ዓይነት ከታወቀ በኋላ ምንም ዓይነት ማስተካከያ ሳይደረግበት ወደዚህ ዓምድ በካርድ ኮለም 71 እና 72 ይተላለፋ ል:: የሕፃኑ ወላጅ እናት በጥናቱ ወቅት የቤተሰቡ አባል ካልሆነች በካርድ ኮለም 71 እና 72 "00" ተብሎ መመዝገብ ይኖርበታል::

### ዓምድ 50:- የሕፃኑ ዕድሜ (በሙሉ ወራት)

ይህ ዓምድ በዓምድ 47 እና 48 መረጃ የተሞላለት ሕፃን ዕድሜ በወራት ተጠ ይቆና ተሰልቶ የሚመዘገብበት ነው:: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ከክፍል 2 ዓምድ 14 የተመዘገበው ዕድሜ በሙሉ በዓመት ስለሆነና ለዚህ ጥናት ግን የሚፈለገው የሕፃ

ኑ ዕድሜ በወራት በመሆኑ የህፃኑ ዕድሜ በወራት ምን ያህል እንደሆነ ቤተሰብ ተጠይቆ መሞላት ይኖርበታል:: ቤተሰቡ የሰጠውን ዕድሜም በክፍል 2 ዓምድ 14 ከተመዘገበው ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ነው:: ሆኖም በክፍል 2 ዓምድ 14 ላይ በዓመት የተሰጠውን ዕድሜ በምንም ዓይነት በ12 በማባዛት ወደ ክፍል 2 ዓምድ 50 ማወራረስ አይቻልም::

ለምሳሌ ቤተሰቡ የሕፃኑ ዕድሜ 4 ዓመት ከ5 ወራት ነው የሚል መልስ ቢሰጥ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለም 73 እና 74 የሚመዘገበው 53=((4x12)+5) ተብሎ ነው:: ሆኖም በክፍል 2 ዓምድ 14 የህፃኑ ዕድሜ በሙሉ ዓመት ስለሚጻፍ 4 ዓመት በመውሰድና በ12 አባዝቶ ማስቀመጥ ምን ያህል ስህተት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል::

ዓምድ 51:- ሕፃኑ ለእናቱ ስንተኛ ልጅ ነው?

በጥናቱ ለተሸፈኑ ሕፃናት በሙሉና በዓምድ 50 ዕድሜአቸው ለተጠቀሰላቸው ለወላጅ እናቱ ስንተኛ ልጅ መሆኑን ወላጅ እናቱን በመጠየቅ ይህ ዓምድ ይሞላል:: ወላጅ እናት የቤተሰብ አባል ካልሆኑና ወላጅ አባት ወይም ለሌላ የቤተሰብ አባል ጥያቄውን አቅርቦ በማያጠራጥር ሁኔታ በትክክል መልስ ማግኘት ካልተቻለ ይህ ዓምድ በሥርዝ "____" ይተላለፋል:: ሕፃኑ ለወላጅ እናቱ ስንተኛ ልጅ ነው በሚባልበትም ወቅት ወላጆች ግልጽ ላይሆንላቸው ስለሚችል፣ ሕፃኑ የመጀመሪያ ወይም የሁለተኛ ወይም የሦስተኛ...ወዘተ ልጅዎ ነውን? በማለትና በመሳሰሉት መንገዶች ማብራራት ተገቢ ነው:: በተጨማሪም ስንተኛ ልጅ ነው ተብሎ ሲቆጠር፣ ሞቶ የተወለደንና ያስወረዳቸውን እንደማይጨምርና በሕይወት የተወለዱትን ወይም በሕይወት ተወልደው የሞቱትን ብቻ እንደሚመለከት መገንዘብ ያስፈልጋል:: በመሆኑም ወላጆች በሕይወት ተወልደው ወዲያው የሞቱትን እንዳይዘነጉ ማስታወስ ተገቢ ይሆናል:: የመንታ ልጆች ውልጃም እንደ አንድ ጊዜ መውለድ ነው መቆጠር ያለበት:: ለምሳሌ:- አንድ እናት የመጀመሪያ እርግዝናቸው ቢያስወርዳቸውና ቀጥሎም በመጀመሪያ መንታ ቀጥሎ ደግሞ አንድ ልጅ ቢወልዱ መንታዎቹ እያንዳንዳቸው እንደ መጀመሪያ "1ኛ" ልጅ ሲቆጠሩ ለብቻው በመጨረሻ የተወለደው ደግሞ እንደ ሁለተኛ "2ኛ" ልጅ ይቆጠራል ማለት ነው:: በዚህ መሠረት ሕፃናት ለወላጅ እናታቸው ስንተኛ ልጅ እንደሆኑ ጠይቆ በማጣራት ለመጀመሪያ ልጅ "1" ለሁለተኛ ልጅ "2" ለሦስተኛ ልጅ "3" ...ወዘተ በማለት በዓምዱ ይመዘገባል:: ነገር ግን ሕፃኑ ለወላጅ እናቱ 8ኛ፣9ኛ፣...ወዘተ ከሆነ የሚመዘገበው "8" ብቻ ይሆናል:: ማለትም 8ኛና ከዚያም በላይ ሲሆኑ የሚሞላው "8" ነው ማለት ነው::

ዓምድ 52 - 55:- ሕፃኑ የ--------ክትባት ወስዷል?

ዕድሜአቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሕጻናት ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ ለ አንዳንድ በሽታዎች መከላከያ የሚሆኑ ክትባቶች መውሰዳቸውን/ አለመውሰዳቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎች በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ ይሰበሰባል። ዕድሜአቸው ከአምስ ት ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት የሚባሉት ጥናቱ በተካሄደበት ቀን ዕድሜአቸው ከ"4 " ዓመት ከ11 ወር ከ29 ቀን የሚደርሰ ሕጻናትና ትናንሽ ልጆችን ያጠቃልላል።

በመጀመሪያ ማንኛውም ዕድሜው/ዋ ከአምስት ዓመት በታች የሞላው/ት ሕ ጻን የፀረ-ስድስት ክትባት/የቢሲጂ፣ የኩፍኝ፣ የዲ.ፒ.ቲ. እና የልምሻ መከላከያ ክትባት / ተደርጎለታል/ተደርጎላታል በማለት በተለይ የሕጻኑ/የሕጻኑዋ እናት ይጠየቃሉ። መልሱ "የለም" ክትባት ተደርጎለት/ተደርጎላት አያውቅም ከተባለ ትክክለኛነቱን በማ ረጋገጥ በዓምድ 52፣ 53፣ 54 እና 55 ኮድ "2" ይሞላል። ለተጠየቀው ጥያቄ መልሰ - "አዎን" ክትባት ተደርጎለታል ከሆነ የክትባት ካርዱን በማየት ትክክለኛነቱ ተጣርቶ ኮድ "1" በእያንዳንዱ ዓምድ ይመዘገባል።

<u>ዓምድ 52 - ሕፃኑ የኩፍኝ /MEASELS/ ክትባት ወስዷል</u>?

ይህ በተለይ ሕጻናትን ስለሚያጠቃው ኩፍኝ ስለሚባለው በሽታ መከላከያ ክት ባት መሰጠቱን ወይም አለመሰጠቱን የሚገልጽ መረጃ ነው። ክትባቱ ለአንድ ጊዜ ብ ቻ የሚሰጥ ነው። ሕፃኑ የኩፍኝ /Measels/ ክትባት ወስዶ ከሆነ የክትባቱን ካርድ በማ የት አረጋግጦ በዓምዱ "1"፣ ካልወሰደ ደግሞ "2" ይመዘገባል። የኩፍኝ በሽታ በአንዳ ንድ የሀገራችን ክፍሎች <u>ወተቴ</u> ተብሎ እንደሚጠራ ማስታወስ ያስፈልጋል።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- የኩፍኝ ክትባት የሚሰጠው በክንድ ላይ ሲሆን ምንም ዓይነት ምልክት/ጠባሳ አያስቀርም።

<u>ዓምድ 53 - ሕፃኑ የቢ.ሲ.ጂ./-BCG/ ክትባት ወስዷል</u>?

ለሳንባ ነቀርሳ መከላከያ /Anti -Tuberculosis/ የሚሆን አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ክትባት ነው። ሕፃኑ የቢ.ሲ.ጂ. /BCG/ ክትባት ወስዶ ከሆነ የክትባት ካርዱን በማየት /የተከተበ ከሆነ/ ኮድ "1" ያል ተከተበ ከሆነ ኮድ "2" በካርድ ኮለም 77 ይመዘገባል።

<u>ማስታወሻ:-</u> የሣንባ ነቀርሳ ክትባት በግራ ትከሻ ላይ የሚሰጥ ሲሆን በግልጽ የሚታይ ጠባሳ የሚተው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 54 - ሕፃኑ የዲ.ፒ.ቲ /D.P.T/ ክትባት ወስዷል?

Diptheria, Pertussis and Tetanus ማለት ለዘጊ አናዳ፣ ለትክትክና ለመንጋጋ ቆልፍ መከላከያ የሚሆን በተወሰነ የጊዜ ርቀት ለሦስት ጊዜ የሚሰጥ ክትባት ነው። ሕፃኑ የዲ.ፒ.ቲ. /D.P.T/ ክትባት ተደርጎለታል ከተባለ የክትባት ካርዱን በመጠየቅ ከተረጋገጠ በኋላ ትክክለኛው ኮድ በካርድ ኮለም 78 ይመዘገባል። ይህ ክትባት የሚሰጠው በሕፃኑ መቀመጫ ወይም ታፋ በኩል ነው። የፀረ-6 ክትባት ካርድ ላላቸው ሕፃናት ይህ ክትባት መሰጠቱ በግልጽ ሰፍሯል።

ዓምድ 55 ሕፃኑ የልምሻ /POLIO/ ክትባት

ለልጅነት ልምሻ /Polio/ መከላከያ የሚሆን በተወሰነ የጊዜ ርቀት ለሶስት ጊዜ የሚሰጥ ክትባት ነው። ሕፃኑ የልምሻ /Polio/ ክትባት ተደርጎለታል ከተባለ የክትባቱን ካርድ በማየት አረጋግጦ በዓምዱ ኮድ "1" ክትባት አልተደረገም ከተባለ ኮድ "2" በካርድ ኮለም 79 ይመዘገባል። የፓሊዮ ክትባት በፈሳሽ መልክ በአፍ የሚሰጥ ሲሆን በ1990 በዘመቻ መልክ ሲሰጥ የነበረ እና ከዚያ በፊትም ክትባቱ ይሰጥ እንደነበር መገንዘብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 56:- ሕፃኑ የቫይታሚን ኤ እንክብሎች ወስዷል?

ለቤተሰቡ የቫይታሚን ኤ /Vitamin A/ ሁለቱን ዓይነት ናሙና እንክብሎች/ካፕሱሎች/ በማሳየት ለሕፃኑ ተሰጥቶ ይታወቅ እንደሆነ በመጠየቅ ትክክለኛው ኮድ በዓምድ 56 በካርድ ኮለም 80 ይመዘገባል።

ዓምድ 57:- ሕፃኑ ባለፉት 14 ቀናት ተቅማጥ፣ ትውከት፣ ሳል ታሞ ነበር?

ባለፉት 14 ቀናት የተጠቀሰው ሕፃን በተቅማጥ ወይም በትውከት ወይም በሳል ሕመም ታሞም ከሆነ ቤተሰቡን በመጠየቅ መልሱ "አዎን" ከሆነ ኮድ "1" "የለም" ከሆነ ኮድ "2" በካርድ ኮለም 81 ይመዘገባል።

ዓምድ 58:- በዓምድ 57 መልሱ አዎን ከሆነ ሕፃኑ ምን ወስዶ ነበር?

በዓምድ 56 ሕፃኑ ተቅማጥ፣ ትውከት፣ ሳል ታምሞ ከነበረ ለህመሙ ማስታገሻ ምን ተሰጥቶት ነበር ተብሎ ተጠይቆ ትክክለኛው ኮድ በካርድ ኮለም 82 ይመዘገባል። አማራጭ የሆኑት መልሶች ከነ ኮዶቻቸው ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። መልሱ ቤት የተዘጋጁ ፈሳሽ ምግቦችና ሌሎች ከሆነ ሕፃኑ ከመታመሙ በፊት ይወስድ ከነበረው በበለጠ መውሰዱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

1 = ኦ.አር.ኤስ(O.R.S)

2 = ቤት የተዘጋጁ ፈሳሽ ምግቦችና ሌሎች ፈሳሾች

3 = ሌላ መድኃኒት

4 = 1 + 2

5 = ምንም አልተሰጠውም

<u>ዓምድ 59:- ሕፃኑ እንደተወለደ ምን ተሰጠው?</u>

ለእያንዳንዱ በጥናቱ የተሸፈነ ሕፃን እንደተወለደ ወዲያውኑ እንዲቀምስ ወዲያውኑ የተደረገው/ የተሰጠው ነገር ምን እንደሆነ ጠይቆ በማጣራት በመጠይቁ በዓምድ 59 በስተግርጌ በተሰጠውና ቀጥሎም ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች በመጠቀም ትክክለኛውን ሁኔታ የሚገልጸውን ኮድ በካርድ ኮለም 83 መመዝገብ ነው:: ይህ ዓምድ በሚሞላበት ጊዜም ወላጆች በአብዛኛው በአንዳንድ ባሕላዊና ልማዳዊ ሁኔታዎች ሕፃናት እንደተወለዱ የሚሰጡዋቸውን ማለትም እንደ ቅቤ ማዋጥ፣ ሙቅ ውሃ ማጠጣት፣...ወዘተ. የመሳሰሉትን ልምዶች ለማወቅ በሚያስችልበት መልኩ አብራርቶ በመጠየቅ ተጣርቶ መሞላት ይገባዋል:: ለሕፃኑ የሚሰጠውም ነገር ለአንድ ጊዜ ብቻ ወይም ለምግብነት በተደጋጋሚና ወደፊትም ሊቀጥል የሚችል ምግብ ሊሆን እንደሚችልም መገንዘብ ያስፈልጋል:: አማራጭ መልሶቹም ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው::

1 = የእናት ጡት ወተት ብቻ

2 = ሙቅ ውሃ

3 = ጥሬ ቅቤ

4 = አብሽ

5 = የእንስሳት ወተት/ሌላ ወተት

6 = ሌላ

<u>ዓምድ 60:- ሕፃኑ እንደተወለደ የእናቱን ጡት መጥባት የጀመረበት ዕድሜ/በሰዓት/</u>

ብዙውን ጊዜ ሕፃናት እንደተወለዱ የእናታቸውን ጡት መጥባት እንደሚጀምሩ ቢገመትም በአንዳንድ ልምዶችና ሁኔታዎች ጥቂት ዘግይተው እንዲጀምሩ የሚደረግበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል:: በመሆኑም በጥናቱ የተሸፈኑ ሕብረተሰቦች በተጠቀሰው ሁኔታ ላይ ያላቸውን ልምድ ለማወቅ በሚያስችል መልኩ እናቶችን ሕፃኑ እንደተወለደ ወዲያውኑ ጡት መጥባት የጀመረበትን ጊዜ በመጠየቅ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ኮዶች አማካኝነት ትክክለኛውን ሁኔታ የሚገልጸውን ኮድ በመምረጥ ኮዱን በካርድ ኮለም 84 እና 85 መመዝገብ ነው:: ወላጆች ሕፃኑ የእናቱን ጡት መጥባት የጀመረበትን ዕድሜ በሰዓት ሲጠይቋቸው መልስ ለመስጠት ሊያዳግታቸው ስለሚችል ጥያቄውን

ለመልስ ሰጪዎች በሚገባ መልኩ በማብራራት ለምሳሌም - ሕፃኑ መጥባት የጀመረ ው ወዲያውኑ እንደተወለደ ነውን? ወዲያውን ካልሆነ ምን ያህል ቆይቶ ነው የጀመ ረው? በማለትና በመሳሰሉት መንገዶች ጥያቄውን በማቅረብና የተሰጠውን መልስ በሰ ዓት ማስላትም እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡ አማራጭ መልሶችም ቀጥ ሎ የተጠቀሱት ናቸው፡፡

1 = አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ

2 = ከ1 - 6 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ

3 = ከ7 - 12 "" "" "" ""

4 = ከ13 - 24"" "" "" ""

5 = ከ25 - 48"" "" "" ""

6 = ከ48 ሰዓት በላይ

7 = ጭራሽ አልጠባም

<u>ዓምድ 61፡- በአሁኑ ጊዜ ሕፃኑ የእናቱን ጡት ይጠባል?</u>
<u>/በዓምድ 60 ከኮድ "1-6" ለመልሱ ብቻ/</u>

በዚህ ጥናት /በዓምድ 60 ከኮድ "1-6" ለመልሱ/ ሕፃኑ ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ የእናቱን ጡት የሚጠባ ወይም የማይበጣ መሆኑነን በተለይ ወላጅ እናቱን ጠይቆ በማጣራት በመጠይቁ ላይ በዓምዱ በተሰጡትና ቀጥሎ በተጠቀሱት አማራጭ መልሶ ች በመጠቀም ትክክለኛውን መልስ የሚያሳየውን ኮድ በካርድ ኮለም 86 መመዝገብ ነ ው፡፡

1 = አዎን 2 = የለም

<u>ዓምድ 62፡- ለዓምድ 61 መልሱ "2" ከሆነ መጥባት ሲያቆም የነበረው ዕድሜ/በወር/</u>

ዕድሜው አምስት ዓመተ በታች ሆኖ የእናት ጡት መጥባት ላቆመ ማንኛው ም ሕፃን /በዓምድ 61 መልሱ "2" ከሆነ/ መጥባት ሲያቆም የነበረው ዕድሜ በሙሉ ወር እዚህ ዓምድ ውስጥ ይፃፋል፡፡ በተለይ ዕድሜአቸው ከ3 እና 4 ዓመት በላይ ለ ሆኑ ሕፃናት ወላጆች ሕፃኑ ጡት መጥባት ያቆሙበትን ዕድሜ በትክክል ማስታወስ ሊ ያስቸግራቸው ስለሚችል ሁኔታው ቀስ ብለው ከልምድም ጭምር እንዲያስታውሱ ማ ገዝ ተገቢ ይሆናል፡፡ ወራትም ሲመዘገብ ከ10 ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ በቁጥሩ በስተግ ራ "0" በመጨመር ባለ ሁለት ዲጂት አድርጎ መመዝገብ አለበት፡፡ ለምሳሌ በ8 ወሩ መጥባት ላቆመ የሚመዘገበው በካርድ ኮለም 87 "0"ን ካርድ ኮለም 88 ደግሞ "8" ባጠቃላይ "08" በማለት ይሆናል፡፡

ዓምድ 63፡- ባለፉት 4 ሳምንታት ለሕፃኑ የተሰጠው የምግብ ዓይነት፡-

በጥናቱ ለተሸፈኑ ሕፃናት በሙሉ ወላጅ እናቶቻቸውን በመጠየቅ ባለፉት 4 ሳ ምንታት ሕፃኑ በአብዛኛው ይመገብ የነበረው ምን እንደሆነ የሚገልጽ መረጃ በዓምዱ ይሰበሰባል፡፡ ባለፉት 4 ሳምንታት ማለት ከሞላ ጎደል ባለፈው ወር ማለት እንደሆነና ለሕፃኑ የተሰጠው ምግብ አንድ ዓይነት ወይም የተቀላቀለ /በተለይ በምግቡ ዝግጅት ና አቀራረብ ወቅት/ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የእናቱን ጡ ት ብቻ ለሚወስድ "የእናት ጡት ብቻ" የሚለውን ኮድ "0"፣ የእናቱን ጡት እየጠባ ባለፉት 4 ሳምንታት ምግብ ለወሰደ በተጨማሪ የወሰደውን የምግብ ዓይነት የሚገልጸ ውን ኮድ በመጠይቁ ዓምድ 63 ግርጌ እና ቀጥሎ ከተዘረዘሩት አማራጮች በመምረጥ በካርድ ኮለም 89 ይመዝገባል፡፡

0 = የእናት ጡት ወተት ብቻ
1 = የእንስሳት ወተት /ሌላ የእንስሳት ውጤት
2 = ጥራጥሬ
3 = እንሥት
4 = አትክልት /ፍራፍሬ/ ሌላ ሥራሥር
5 = 1 + 2 ወይም 1 + 3 ወይም 1 + 4
6 = 2 + 3 ወይም 2 + 4
7 = 3 + 4
8 = ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ/ድብልቆች

ዓምድ 64፡- ለዓምድ 63 መልሱ "0" ካልሆነ ሌላ መመገብ ሲጀምር የነበረውዕድሜ /በወር/፡-

ዕድሜው ከ3 ወር እስከ 59 ወር ሆኖ በጥናቱ ለተሸፈነ ሕፃን ሁሉ በጥናቱ ወ ቅት ከእናቱ ጡት ወተት ሌላ መውሰድ ጀምሮ ከሆነ ማለትም የእናቱ ጡት ወተት ብቻ በመጥባት የሚኖር ካልሆነ ከእናቱ ጡት ወተት ሌላ መመገብ የጀመረው መቼ እንደሆነ ይጠይቃል፡፡ ሌላ ምግብ መመገብ የጀመረው ሙሉ በሙሉ የእናቱን ጡት አቁሞ፣ ወይም ከእናቱ ጡት በተጨማሪነት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት ሕፃኑ ከ እናቱ ጡት ሌላ ምግብ መውሰድ ሲጀምር የነበረው ዕድሜ በተለይ ወላጅ እናትን በ መጠየቅ የተገኘው መልስ በሙሉ ወር በካርድ ኮለም 90 እና 91 ይመዘገባል፡፡ ወሮ ች በሚመዘገቡበትም ጊዜ ቀደም ሲል በዓምድ 62 እንደተደረገው ከ10 ወር ላነሰ በስ

ተግራ በኩል "0"ን በማስገባት ባለ ሁለት ዲጂት አድርጎ መመዝገብ እንደሚገባ መዘ ንጋት የበለትም።

## ዓምድ 65፡- ስለ ሕፃኑ ዕድገት ሁኔታ የእናት አስተያየት፡-

የሕፃኑ እናት አካላዊ-አስተዳደጉን በተመለከተ ያላቸውን አስተያየት በመጠየቅ በመጠይቁ ላይ በዓምዱ ግርጌ ከ1-3 ከተሰጡትና በድጋሚም ቀጥሎ ከተዘረዘሩት አ ማራጭ መልሶች የእናቱን አሰተያየት የሚገልጸው ትክክለኛውን ኮድ መርጦ ኮዱን በ ካርድ ኮለም 92 መመዝገብ ነው። ሆኖም የሕፃኑ አስተዳደግ ሲባል ምን ማለት እን ደሆነ ማብራራት የሚያስፈልግበትም ጊዜ መኖሩን አለመዘንጋት ነው። ማለትም የሕ ፃኑ አስተዳደግ ሲባል ከታላላቆቹ የአስተዳደግ ሁኔታ ጋር በማወዳደር ወይም ከእኩዮ ቹ ያስተዳደግ ሁኔታ ጋር እና ከመሳሰሉት ሁኔታዎች ጋር በማወዳደር አስተዳደጉ ም ን ይመስሎታል ብሎ ለእናቶች አብራርቶ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። አማራጭ መልሶ ቹም፡-

1 = ትክክለኛ ዕድገት ነው

2 = ትክክለኛ ዕድገት ያልሆነ ነው

3 = አያውቁም

## ዓምድ 66-67 የሕፃናት ክብደትና ቁመት አለካክ መመሪያ/ዕድሜያቸው 3ወር እስከ 59ወር ለሆናቸው ሁሉ/

ከ3ወር እስከ 59 ወር ባለው የዕድሜ ገደብ ውስጥ የሆነ የማንኛውም ሕፃን ቁ መትና ክብደት በትክክል ተለክተው በእነዚህ ዓምዶች ይሰፍራሉ። ይህም ሲሆን ክብ ደት የሚለካው በባለ ሞላ ሚዛን /Spring Balance/ ቁመት ደግሞ በእግር መቆሚያ የተሠራ መለኪያ ይሆናል።

የቁመትና ክብደት ልኪት በሚደረግበት ጊዜ የሕፃናትን ልቀሶ ለመቀነስና ተባ ባሪነታቸውን ከፍ ለማድረግ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ መለካት ያስፈልጋል። በአ ንድ ቤተሰብ ውስጥ መለካት ያለባቸውን ሕጻናት በሙሉ በመጀመሪያ ከትልቁ ወይም ተባባሪ የሆነውን ቁመት በመለካት መጀመርና ሌሎችንም ልጆች በማግባባት መለካት

ን መቀጠል፣ ከዚያም ሁሉንም በዚሁ ቅደም ተከተል ክብደታቸውን መለካት ነው፡፡ በቤተሰቡ መካከል ጥናቱ ከሚመለከታቸው ሕጻናት ውስጥ እሺ ብሎ የሚለካ ሕፃን ከ ጠፋ ከ5 ዓመት በላይ የሆነ ትንሽ ልጅ ካለ ሕፃኑ እሱን ተባባሪ እንዲሆን ለማድረግ ይህን ትንሽ ልጅ በመለካት መጀመር የሚያስፈልግበት ጊዜም ሊኖር ይችላል፡፡ ስለዚ ህ ካስፈለገ በቅርብ ጎረቤት ውስጥ የሚገኝ ትንሽና ተባባሪ የሆነ ልጅን ለክቶ ለማይተ ባበሩ ሕጻናት በማሳየት መጀመር ይቻላል፡፡ ነገር ግን በተለይ ክብደትን በሚመለከት ለማግባባት ተብሎ ሌሎች ጥናቱ የማይመለከታቸውን መመዘን ሚዛኑን ሊያበላሽ ስለ ሚችል ከእንዲህ ዓይነቱ ተግባር መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ሕጻኑን ለማግባባት የክብደት መለኪያውን ሱሪ ልጁ እንዲያጠልቅ አድርጎ በሚዛኑ ላይ ሳያንጠለጥሉ ክብ ደቱን የሚለካ ለማስመሰል ይችላል፡፡

የሕጻኑን ዕድሜ ከሁለት ዓመት በታች ከሆነ የሕጻኑ ቁመት የሚለካው ከመለከ ያ መሣሪያው ላይ ቀጥ አድርጎ በጀርባው በማስተኛት የሕጻኑን ርዝመት በመለካት ይሆናል፡፡ ዕድሜው ሁለት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነውን ሕጻን ደግሞ ቁመቱ የሚለካው ሕጻኑን ከመለኪያው መቆሚያ ላይ እግሩን ገጥሞ ቀጥ አድርጎ በማቆም የሕጻኑን ቁመት በመለካት ይሆናል፡፡

እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት ማለትም የክብደቱና የቁመቱ ልኪት የሚደረግ አ ስቀድሞ ሌላው የመጠይቁ ክፍል ከተሞላ በኋላ ነው፡፡

<u>ዓምድ 66፡- ክብደት በግራም /ዕድሜያቸው 3ወር እስከ 59ወር ለሆናቸው ሕፃናት</u>

ለማንጠልጠያ እንዲረዱ ተብሎበተሰጡት መንጠቆዎች /hook/ በመጠቀም ሚዛ ኑ በማይነቃነቅ እንጨት ወይም ሌላ ነገር ላይ እንዲንጠለጠል ከተደረገ በኋላ ሕፃኑ ል ብሱን አውልቆ ለዚህ ሥራ እንዲጠቅም የተሰጠውን ሱሪ እንዲያጠልቅ አድርጎ በሚዛ ኑ ላይ በማንጠልጠል ክብደቱን በትክክል መለካት ነው፡፡

<u>ማሳሰቢያ፡-</u>

ማንኛውም ሕጻን ክብደቱን ሲለካ ወድቆ እንዳይጎዳ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ ሚዛኑ የክብደት መመዘኛው ሱሪ ተንጠልጥሎበት "0" የሚል ንባብ የሚያ ሳይ መሆኑን <u>በየጊዜው ማረጋገጥ /ካስፈለገም ማስተካከል/ ያስፈልጋል</u>፡፡ በዚሁ መሠ ረት ይህ ዓምድ ዕድሜያቸው ከ3-59 ወራት የሆናቸው ሕፃናት በሙሉ ለዚህ ጥናት

በተዘጋጀው ሚዛን በመመዘን ክብደት <u>በግራም</u> በካርድ ኮለም 93 እስከ 97 ይመዘገባል ::

<u>ማስታወሻ</u>፡- 1 ኪሎ ግራም 1000 ግራም መሆኑ መረሳት የለበትም:: ለክብደት መ መዝገቢያ የተሰጡት ካርድ ኮለሞች 5 በመሆናቸው የሕፃኑ ክብደት ከ10 ኪሎግራም በታች /ከ10000 በታች/ ከሆነ በቁጥሩ በስተግራ "0" በመጨመር ባለ 5 ዲጂት አድ ርጎ መመዝገብ ያስፈልጋል:: ለምሣሌ የሕፃኑ ክብደት 5 ኪሎግራም ከ545 ግራም ከ ሆነ በዓምድ የሚመዘገበው "05545" ነው እንጂ "5545" ተብሎ/ አንድን ካርድ ኮለ ም ባዶ በመተው/ አይመዘገብም::

<u>ዓምድ 67 ቁመት በሴንቲ ሜትር /ዕድሜያቸው 3ወር እስከ 59 ወር ለሆናቸው ሕፃናት/</u>

ለማንኛውም <u>ዕድሜው ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ሕጻን</u> የቁመት መለከ ያውን ከግድግዳ አስጠግቶ ጠፍጣፋ መሬት ላይ ማቆምና ከዚያም ሕፃኑን ማቆሚያ ው ላይ እግሩን ገጥሞ ቀና አርጎ በማቆም ኳድሮው የሕፃኑን አናት እስኪነካ ከላይ ቀ ስ ብሎ ጫን ማለት ቁመቱ በትክክል በሙሉ ሴንቲ ሜትር አንብቦ መመዘገብ ያስፈል ጋል:: ሕፃኑ ቀጥ ብሎ ሲቆም ተረከዙ ራሱና መላ ቁመቱ ሳይጎብጥ ሜትሩ የተለጠ ፈበትን እንጨት መንካት ያለባቸው ከመሆናቸውም በላይ እገሮቹ ፍጹም ቀጥ ያሉ ወ ይም የተገተሩ መሆን ሲገባቸው የሕፃኑ እይታ ፊት ለፊት ቀጥ ያለ መሆን አለበት:: ይህም ማለት ሕፃኑ መሬት መሬት ሳያይ ወይም ወደ ላይ ሳያንጋጥጥ ማለት ነው::

ለማንኛውም <u>ዕድሜው ከሁለት ዓመት በታች ለሆነ ሕጻን</u> ደግሞ ቁመቱ የሚ ለካው የቁመት መለኪያውን ወጣ ገባ በሌለበት ጠፍጣፋና ጠንካራ ከሆነ ወለል፣ ጠረ ጴዛ፣...ወዘተ. ላይ በማስተኛት ከዚያም ሕጻኑን በመደገፍ በመለኪያ መሣሪያው ላይ የ ሕጻኑን ጭንቅላት/አናት ወደ መለኪያ መሣሪያው መቆሚያ በማድረግ ቀጥ አድርጎ በ ጀርባው በማስተኛት ነው:: ልኪቱም ከመነበቡ በፊት የሕጻኑ አናት የመለኪያ መሣሪ ያውን መቆሚያ በሚገባ ማስነካትና የሕጻኑን ጆሮ ግንድ በእጅ ደግፎ ሕፃኑ በሚገባ ወደ ላይ መመልከቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በመጨረሻ የሕጻኑን እግሮች አንድ ላይ ገጥሞ ቀጥ ብለው የተዘረጉ መሆናቸውን ጉልበቱን በእጅ በመጫንና እግሮቹን በእጅ በመግጠም ጭምር ካረጋገጡ በኋላ ኳድሮው መሐል ለመሐል ማስረገጥና ትክክለኛው ን መመዘገብ ነው:: ርዝመቱ በሚመዘገብበት ጊዜ የሕጻኑ ቁመት ከ100 ሳንቲ ሜትር ያነሰ ከሆን በቁጥሩ በስተግራ "0" በመጨመር ባለ ሦስት ዲጂት ቁጥር አድርጎ መጻ ፍ አለበት:: ለምሳሌ የሕፃኑ ቁመት 76 ሳንቲ ሜትር ቢሆን የሚመዘገበው "076" ሳ ንቲ ማትር ነው::

በዚህ ዓምድ /ዓምድ 67/ የሕፃኑ ቁመት ለዚሁ በተሰጠው የቁመት መለኪያ ተለክቶ በሳንቲ ሜትር ከካርድ ኮለም 98-100 ባለው ይመዘገባል፡፡ ሕፃኑን ለመለካት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ማስታወሻ 1 ሜትር 100 ሳንቲ ሜትር ነው፡፡

–

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቨይ ፕሮግራም የወሊድና የሞት ሁኔታ /1990/

<u>ክፍል -1፡-</u> የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

<u>ዓምድ 1-8፡-</u> የአካባቢ መለያ

በዚህ ዓምድ ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከ ተማ፣ ክፍተኛ/ወረዳ፣ ቀበሌ/ገበሬ ማኀበርና የቆጠራ ቦታና የተመረጠው ቤተሰብ የ ምርጫ ተራ ቁጥር ይመዘገባል፡፡

<u>ዓምድ 9፡- የተመረጠው ቤተሰብ አባላት ብዛት</u>

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ አባላት ብዛት ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለ ም 21 እና 22 ውስጥ ይሞላል፡፡ በቤተሰብ ምን ማለት እንደሆነ በጤናና አመጋገብ ጥናት ክፍል 1 ዓምድ 9 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

<u>ዓምድ 10፡- የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም</u>

በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ኃላፊ የቤተሰቡ መደበኛ አባል የሆነና በቤተሰቡ አባላ ት እንደ ኃላፊ የሚቆጠር/የሚታይ/ ሰው ስም ተጠይቆ ይመዘገባል፡፡

<u>ዓምድ 11፡- ተራ ቁጥር</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው ከጤናና አመጋገብ ጥናት ክፍል 2 ዓምድ 11 ላይ የተ መዘገበውን የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር በመውሰድ ይሆናል፡፡

<u>ዓምድ 12፡- የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም</u>

የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም ከጤናና አመጋገብ መጠይቅ ክፍል 2 ዓ ምድ 12 በመውሰድ ይሞላል፡፡

<u>ዓምድ 13፡- ፆታ</u>

በዓምድ 12 ስማቸው ለተላለፈላቸው የቤተሰቡ አባላት ፆታ ከጤናና አመጋገ ብ ክፍል 2 ዓምድ 13 በመውሰድ ይሞላል፡፡

<u>ዓምድ 14፡- ዕድሜ (በሙሉ ዓመት)</u>

በዓምድ 12 ስማቸው ለተመዘገበው የቤተሰብ አባላት ዕድሜ ከጤናና አመጋገ ብ መጠይቅ ክፍል 2 ዓምድ 14 በመውሰድ የሚመዘገበው ነው።

ዓምድ 15፡- የጋብቻ ሁኔታ

በዓምድ 12 ስማቸው ለተመዘገበው መደበኛ የቤተሰብ አባላት የጋብቻ ሁኔታ ከጤናና አመጋገብ መጠይቅ ክፍል 2 ዓምድ 18 በመውሰድ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለ ም 28 ይሞላል። በዚህ ዓምድ የጋብቻ ሁኔታ የሚሞላላቸው ዕድሜያቸው 15 ዓመ ትና በላይ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት ሁሉ ስለሆነና በጤናና አመጋገብ መጠይቅ የጋብቻ ሁኔታ የሚሞላው ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ በመሆኑ፣ የጋብቻ ሁኔታ መረጃ በሚወራረስበት ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም ማለት ከጤናና አመጋገ ብ መጠይቅ ክፍል 2 ዓምድ 18 የጋብቻ ሁኔታ የሚወራረስላቸው ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ ለሆነ የቤተሰብ አባላት ብቻ ነው።

ክፍል 2 አሥራ አምስት ዓመትና በላይ ለሆናቸው ሴቶች ሁሉ የሚጠየቅ

ዓምድ 16 - 19፡- በጠቅላላ በሕይወት የወለዷቸው ልጆች ብዛት

በዓምዶቹ ተፈላጊ መረጃዎች ከመመዝገባቸው በፊት « በሕይወት ተወለደ» ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት ያስፈልጋል። "በሕይወት ተወለደ" ማለት አን ድ ፅንስ በማህፀን የቆየበት ወራት በግምት ውስጥ ሳይገባ ከእናቱ ማህፀን በሚወጣበት ወቅት የሚተነፍስ ከሆነ ወይም እትብቱ ከመቆረጡ በፊት ወይም ከተቆረጠ በኋላ ሌ ላ ዓይነት በሕይወት የመኖር ምልክት ካሳየ ለምሣሌ የልብ ትርታ፣ የእትብት ትርታ፣ የጡንቻዎች እንቅስቃሴ በሕይወት የተወለደ ይባላል። እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈ ልገው የሕይወት ምልክት አሳይቶ ወዲያውኑ ቢሞት እንኳን በሕይወት እነደተወለደ መቆጠሩንና የእርግዝና ወቅት መርዘም ሆነ ማጠር ከግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱን ነው ። ሆኖም ግን ውርጃና በማህፀን ውስጥ ሞቶ የተወለደ በሕይወት እንደተወለደ ስለማ ይቆጠር አይመዘገብም። እንዲሁም የማደጎ ልጆች ወይም ያሳደጓቸው ልጆች እንደወ ለዷቸው ልጆች አይቆጠሩም።

ዓምድ 16፡- አሁን እቤት የሚኖሩ ልጆች ስንት ናቸው?

ዕድሜያቸው 15 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሴቶች በጠቅላላ በሕይወት ከወለ ዷቸው ልጆች መካከል ስንቱ ሴትየዋ ከመትኖርበት ቤተሰበ ጋር እንደሚኖሩ በመጠየ ቅ የልጆቹን ብዛት በጾታ በመለየት በዓምድ 13 በካርድ ኮለም 29 የወንዶች ብዛት ሲ መዘገብ በካርድ ኮለም 30 የሴቶች ብዛት ይመዘገባል። በዚህ ዓምድ ውስጥ መጠቃለ

ል የሚገባቸው መልስ ሰጪዋ አሁን በጋብቻ የሚገኙ ከሆነ አብረዋቸው ከሚኖሩት ባ ለቤታቸው ወይም ከዚህ ጋብቻ በፊት አግብተው የሚያውቁ ከሆነ ከቀድሞ ጋብቻቸ ው የወለዷቸውን ልጆችና በአሁኑ ወቅት አብረው በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩት ን ሲሆን በተጨማሪም ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ልጆችንም ይጨምራል፡፡ ሆኖም ግን ከአብራካቸው ያልወጡትን (ለምሣሌ በጋብቻ ላይ ላሉ ሴቶች ባለቤታቸው ከሌላ ሴት የወለዱትንና፣ የክርስትና ልጅ) ግን አያጠቃልልም፡፡ አስራ አምስት ዓመትና ከላይ ለሆኑ ሴቶችና ልጅ ወልደው ለማያውቁ በዚህ ዓምድ እና በሚቀጥሉት ሦስት ዓምዶ ች ውስጥ ሁሉ ዜሮ "0" ይሞላል፡፡ በሕይወት ከተወለዱ ልጆች ውስጥ አሁን ከቤተሰበ ‑ ጋር እቤት የሚኖሩ የወንዶች/ሴቶች ልጆች ብዛት ከ8 በላይ ከሆነ ዓምድ 17 ከ8 በ ላይ የሆነው ሌላ ቦታ የሚኖሩ ልጆች ጋር ተደምረው ከተመዘገቡ በኋላ በቅጹ ግረጌ ስነቱ /በፆታ በመለየት/ዓምድ 17 ባሉት ላይ ተደምሮ እንደገባ ማስታወሻ መጻፍ ያስ ፈልጋል፡፡

ዓምድ 17፡ አሁን ሌላ ቦታ የሚኖሩ ልጆችዎ ስንት ናቸው?

በጠቅላላው በሕይወት ከተወለዱ ልጆች መካከል ስንቶቹ ሌላ ቦታ እንደሚኖሩ ጠይቆ በጾታ በመለየት በዓምድ 14 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል፡፡ በሕይወት ከወ ለዷቸው ልጆች መካከል ሌላ ቦታ የሚኖሩ ከሌሉ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለሞች ውስጥ ዜሮ "0" ይሞላል፡፡ ሌላ ቦታ የሚኖሩ የወንዶች/የሴቶች ብዛት ከ8 ከበለጠ ካርድ ኮ ለሙን ባዶ በመተው በመጠይቁ ግረጌ የሴትዩዋ ተራ ቁጥርና ሌላ ቦታ የሚኖሩ ልጆ ች ብዛት በፆታ በመለየት ማስታወሻ ይጻፋል፡፡

ዓምድ 18፡- የሞቱ ልጆችዎ ስንት ናቸው?

በጠቅላላው በሕይወት ከተወለዱ ልጆች መካከል ስንት እንደሞቱ ተጠይቆ የሞ ቱትን ልጆች ብዛት በዓምድ 18 በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ መሙላት ያስፈልጋ ል፡፡ በሕይወት ተወልደው የሞቱ ልጆች ከሌሉ ግን በዚህ ዓምድ የሚገኙ ካርድ ኮለ ሞች ውስጥ ዜሮ "00" ይሞላል፡፡ ይህ ዓምድ በሚሞላበት ጊዜ የሞቱ ልጆች ሲባል በሕይወት ከተወለዱ በኋላ የሞቱትን እንጂ ሞተው የተወለዱትን እንደማይጨምር ማስ ታወስ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪ በጠቅላላ በሕይወት ከተወለዱት መካከል የሞቱ ወንድ ልጆች ቁጥር ከ8 በላይ ከሆነ የሞቱት ወንድ ልጆች ብዛት በሴቶች ላይ በመደመር ከ8 በላይ የሆነውን ከተመዘገበ በኋላ በገጽ መጨረሻ ላይ ማስታወሻ መጻፍ ያስፈልጋል፡፡ የሴቶች ቁጥር ከ8 በላይ ከሆነም በተመሳሳይ መልክ መመዝገብ አለበት፡፡

ዓምድ 19፡- በጠቅላላው በሕይወት የወለዷቸው ልጆችዎ ስንት ናቸው?

በዚህ ዓምድ ስር በተሰጡት ካርድ ኮለሞች መልስ ሰጪዎች በጠቅላላ በሕይወ ት የወለዷቸው ልጆች ብዛት ተጠይቆ ይመዘገባል:: ሆኖም ግን እዚህ ላይ ማረጋገጥ የሚያስፈልገው እቤት የሚኖሩ፣ ሌላ ቦታ የሚኖሩና የሞቱ ተደምረው በጠቅላላ በሕ ይወት የተወለዱ ከሚለው ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል:: ይህ ካልሆነ ግን እንደገና መልስ ሰጪዋ ጥያቄውን በማቅረብ ማስተካከል ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 20-21:- ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ልጅ ስለመውለድና የልጁ በሕይወት የመ ኖር ሁኔታ:-</u>

ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ የሆኑ ሴቶች ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ልጅ በሕይወት የወለዱ መሆኑ ተጠይቆ በዓምድ 20 እና 21 ውስጥ ትክክለኛው መልስ ይ መዘገባል:: በተጨማሪም "<u>ባለፉት 12 ወራት</u>" ማለት ከጥናቱ ቀን በፊት የነበሩትን 1 2 ወራት መሆኑን መልስ ሰጪው በትክክል መረዳት አለባቸው ለምሳሌ ጥየቱ የሚካሄ ደው ሚያዝያ 8 ቀን 1990 ከሆነ ባለፉት 12 ወራት የሚለው ጊዜ የሚመለከተው ከሚያዝያ 7 ቀን 1990 እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1989 ያለውን ጊዜ ነው::::

<u>ዓምድ 20:- ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ልጅ ከወለዱ የወለዱዋቸው ልጆች ብዛት ካል ወለዱ "0" ይሞላ</u>

በዚህ ዓምድ ውስጥ መልስ ሰጪዎች ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ሕይወት ያለ ው ልጅ ወልደው የነበረ መሆናቸው ተጠይቆ ልጅ ወልደው ከነበረ ብዛታቸው በተስ ማሚው ካርድ ኮለም ውስጥ ይመዘገባል:: ሕይወት ያለው ልጅ መውለድ ማለት ምን ማለት እነደሆነ ከላይ ለዓምድ 16-19 በተሰጠው ማብራሪያ የተጠቀሰውን ትርጉም መመልከት አስፈላጊ ነው መልስ ሰጪዋ ባለፉት 12 ወራት ሕይወት ያለው ልጅ ከወ ለዱ የልጆቹ ብዛት በዚህ ዓምድ ሲሞላ ሕይወት ያለው ልጅ ካልወለዱ ግን «0» ይ ሞላል:: ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ልጅ የወለዱ ሴቶች ቢያጋጥሙ በአብዛኛው በዓመ ት ውስጥ የሚወለደው አንድ ልጅ ስለሆነ ለነዚህ ሴቶች «1» ይመዘገብባቸዋል:: ነገር ግን በአጋጣሚ መንታ ለወለዱ ወይም በዓመት ውስጥ ደግመው ለወለዱ ሴቶች «2 »/ እንደ ሁኔታው ከዚያ በላይም ሊሆን ከቻለ/ ይሞላላቸዋል:: ምንም እንኳ ይህ ዓ ምድ የሚጠየቀው ለአሥር ዓመትና በላይ ለሆኑ ሴቶች ሁሉ ቢሆንም የመውለጃ ጊዜ ያቸው ላለፈባቸው በዕድሜ የገፉ ሴቶች ሁሉ ቢሆኑም የመውለጃ ጊዜያቸው ላለፈባ ቸው በዕድሜ የገፉ ሴቶች /50 ዓመትና በላይ የሆናቸው/ ባለፉት 12 ወራት ልጅ ወልደው ነበር የሚል መረጃ እንዳትጽፍ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ለእነዚህ ሴቶች ሁሉ የሚመዘገብላቸው መልስ «0» ይሆናል:: ሆኖም ግን ዕድሜያቸው ከ50 ዓመት በላይ ሆኖ ልጅ መውለዳቸው ከተረጋገጠ የወለዱት ልጆች ብዛት ይመዘገባል:: በተጨማሪም ዓምድ የሚመዘገበው ባለፉት 12 ወራት የተወሰዱት ልጆች ብቻ ስለሆነ አንዳንድ መ

ልስ ሰጪዎች በጠቅላላው የወለዱአቸውን ልጆች ሁሉ እንዲያስመዘግቡ መጠንቀቅ ያ ስፈልጋል።

<u>ዓምድ 21፡- ባለፉት 12 ወራት ከተወለዱት ልጆች ውስጥ ስንቱ ሞተዋል?</u>

በዚህ ዓምድ ውስጥ መረጃ የሚሰበሰብላቸው ባለፉት 12 ወራት ሕይወት ያለ ው ውስጥ ልጅ ወልደው ለነበረና በካርድ ኮለም 37 ከ"0"የተለየ ለተመዘገበላቸው ብ ቻ ነው። ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በሕይወት ከተወለዱት ልጆች መካከል ስንቱ እን ደሞቱ ተጠይቆ በካርድ ኮለም 38 ውስጥ ይመዝገብ። ነገር ግን ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ልጅ በሕይወት ላልወለዱ ይህ ዓምድ ይዘለላል።